ከፍታ የወጣቶች ኃ/የተወሰነ መሰረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራማህበርመተዳደሪያ ደንብ

ነሐሴ 2015

አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
መዝገብ ቤት
Archive
Ethiopian Cooperative Commission Archive

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Kefeta Youth Primary SACCO Ltd.Liab

ከፍታ የወጣቶችኃ/የተወሰነ መሰረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበርመተዳደሪያ ደንብ

አንቀጽ 1 የኅብረት ሥራ ማህበሩ ስም፤ አድራሻና የስራ ክልል

1.1. የኅብረት ሥራ ማህበሩ ስም

ከፍታ የወጣቶች ኃ.የተመሰረታዊ የገንዘብ ቁጠባ እና ብድር. ኅብረት ሥራ ማህበር

1.2. የኅብረትሥራ ማህበሩ ዋና ጽ/ቤት አድራሻ፤-

1.2.1. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለሎ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 የቤት ቁጥር አዲስ ነው፡፡

1.2.2. ስልክቁጥር____________ወይም____________

1.2.3. ኢሜል፡____________

1.2.4. ድረ-ገፅ፡____________

1.2.5. ፓ.ሣ.ቁ________አዲስአበባ፡፡ ዋና መ/ቤቱም አዲስ አበባ ኢትዮጲያ ይሆናል፡፡

1.3. የኅብረት ስራ ማህበሩ የስራ ክልል

የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ ክልል አዳማ፣ አዲስ አበባ፣ ጅማ፣ ሻሸመኔ፣ ሀዋሳ፣ ደብረ ብርሃን፣ ኮምቦልቻ፣ ደሴ፣ ዲላ፣ ድሬደዋ፣ ሀረር፣ ቢሾፍቱ፣ድሬደዋ፣ ጅግጅጋ፣ ሰመራ፣ መቀሌ፣ ጋምቤላ እና አሶሳ ሆኖ በተጠቀሱት ከተሞች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ይኖረዋል፡፡

1.4. የኅብረት ስራ ማህበሩ አርማ

የኅብረት ሥራ ማህበሩ አርማ፤ወጣቶች ተያይዘው በትልቅ ተራራ ላይ ሲወጡ የሚያሳይ ምስል ሲሆን ትርጉሙም አካታችነት ባለው መልኩ በአንድ ላይ በመተባበር ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮችን በጋራ በማሸነፍ ለስኬት መድረስን ያመለክታል፡፡

1.5. የኅብረት ስራ ማህበሩ ማህተም እና አጠቃቀም

1.5.1 የኅብረት ሥራ ማኅበሩ ማህተም ሁለት ክቦችን ከውጭና ከውስጥ የያዘ ሲሆን በትልቁ ክብ በውስጠኛው ክፍል በላይኛው አጋማሽ በውስጡ የኅብረት ሥራ ማኅበሩን ስም በእንግሊዘኛ የሚፃፍበት ሲሆን በታችኛው አጋማሽ ደግሞ የኅብረት ሥራ ማኅበሩን ስም በአማርኛ የሚፃፍበትይሆናል፡፡ በፅሁፎቹ አካፋይ በግራና በቀኝ በኩል ኮኮቦች ይኖሩበታል፡፡በተጨማሪም በትንሿ ክብ ውስጥ የኅብረት ስራ ማህበሩ አርማ ይቀመጣል፡፡

1.5.2. የኅብረት ሥራ ማህበሩ ከፍታየወጣቶች ኃ.የተ. መሰረታዊ የገንዘብ ቁጠባ እና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር የሚል ለዋናው መስሪያ ቤት ክብ ቅርጽ ያለው ማህተም ሲኖረው ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን መዝገብ ቤት Archive Ethiopian Cooperative Commission Archive

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Kefela Youth Primary SACCO Ltd.Hub

አራት ማህዘን ቅርፅ ያለው ማህተም ሆኖ የቅርጫፍ ጽ/ቤቱን ስም እንደ አስፈላጊነቱ በክልሉ ቋንቋሊጠቀም ይችላል፡፡

1.5.3የኅብረት ስራ ማህበሩ ዋና ጽ/ቤት ማህተም የሚያገለግለው የኅብረት ስራ ማህበሩ የሚያደርጋቸውን የተለያዩ የስራ እንቅስቃሴዎችና የሚፈጽማቸው ውሎችን ለማረጋገጥ ስራ ላይ መዋል አለበት፡፡

1.5.4የኅብረት ስራ ማህበሩ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ማህተም የሚያገለግለው የቅርጫፍ ጽ/ቤቱን የብድር ውል ለማጽደቅ፣ ደብዳቤዎችና ሪፖርቶችን ለዋና ጽ/ቤት አረጋግጦ ለመላክእንዲሁም በስራ አካባቢያቸው ከሚገኙ አጋር አካላት ጋር የሚያደርጉትን የደብዳቤ ልውውጥ ለማረጋገጥ ስራ ላይ መዋል አለበት፡፡

ትርጉም

በአዋጅ 985/2009 እና የኅብረት ስራ ማህበራት አደረጃጀት መመሪያ ቁጥር 896/2014 የተቀመጠው ትርጓሜ እንዳለ ሆኖ የቃሉ አገባብ በህግ ሌላ ትርጉም የማያሰጥ ካልሆነ በስተቀር በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ፡-

3.1 "ግለሰብ" ፡-ማለት በህግ መብት የተሰጠው የተፈጥሮ ሰው ማለት ሲሆን ይህም የወንድን ወይም የሴትን ጾታ የሚያካትት ነው፡፡

3.2 "ሸሪዓ" ማለት የእስልምና ተከታዮች የሚመሩበት ህግና ድንጋጌ ማለት ነው፡፡

3.3 "መደበኛ ቁጠባ" ማለት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበሩ በሚወስነው የጊዜ ገደብ እና ዝቅተኛ የገንዘብ መጠን መሰረት በማድረግ አባሉ በግሉ የወሰነውን የቁጠባ መጠን በተከታታይነት ያለማቋረጥ የሚቆጠበው ቁጠባ ነው፡፡

3.4 "የፍላጎት ቁጠባ" ማለት አባሉ በፍላጎቱ ከመደበኛው ቁጠባ በተጨማሪ በተለያዩ የቁጠባ አይነት የሚቆጠበው ቁጠባ ነው፡፡

3.5 "የልጆች ቁጠባ" ማለት እድሜያቸው ከ18 አመት በታች የሆኑና በኅብረት ሥራ ማህበሩ የስራ ክልል የሚኖሩ ልጆች በቤተሰቦቻቸው በኩል የሚቆጥቡት የአደራ ቁጠባ አይነት ነው፡፡

3.6 "ብድር" ማለት አባላት ለተለያዩ ጉዳዮች ማስፈጸሚያ የሚሆን ከገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ወይም ከፋይናንስ ተቋማት በሚደረግ ስምምነት መሰረት በተወሰነ ጊዜ ቆይታ ተመላሽ የሚሆን እና ወለድ የሚያስከፍል ወይም ወለድ የማያስከፍል ገንዘብ ነው፡፡

3.7 "ወለድ" ማለት ግለሰቦች ወይም ተቋማት ለቆጠቡት ገንዘብ የሚከፈላቸው ወይም ለተበደሩት ገንዘብ የሚከፍሉት ዋጋ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
መዝገብ ቤት
Archive
Ethiopian Cooperative Commission Archive
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Kefeta Youth Primary SACCO Ltd.

3.8 “ወለድ የሚያስገኝ የፋይናንስ አገልግሎት” ማለት የቁጠባ እና የብድር የፋይናንስ አገልግሎት ሆኖ ቆጣቢዎች ወለድን የሚያገኙበት ወይም ተበዳሪዎች ወለድ የሚከፍሉበት አገልግሎት ነው፡፤

3.9 “ወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት” በሸሪዓ መሰረት በሚሰጡ የቁጠባና የብድር አገልግሎቶች ወለድ መቀበልና መክፈልን በጥብቅ የሚከለክል አገልግሎት ማለት ነው፡፡

3.10 “ተካፉል አገልግሎት” ማለት በሸሪያ መሰረት የሚሰጥ የአነስተኛ መድን ዋስትና አገልግሎት ነው፡፡

3.11 “አረቦን” ማለት ለአነስተኛ መድን ዋስትና ወይም ተካፉል አገልግሎትን ለመስጠት እንዲቻል ከተበዳሪ የሚሰበሰብ ገንዘብ ነው፡፡

3.12 “ተጨማሪ እጣ” ማለት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር ለተለያዩ ኢንቨስትመንት ስራዎች ለማከናወን ለአባላት የሚሸጠው እጣ ነው፡፡

3.13 “መነሻ እጣዎች” ማለት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር አባል መሆን ሲፈልግ ሙሉ አባል ለመሆን የሚገዛው እጣ ነው፡፡

3.14 “የአባላት ካፒታል” ማለት አንድ አባል የገዛው የዕጣ መጠን እና የመደበኛውን ቁጠባ ደህንነት ለመጠበቅ በሚያስችል ምጥጥን ተሰልቶ አባሉ የሚያስቀምጠው ገንዘብ ነው፡፡

3.15 “የፋይናንስ አገልግሎት አካታችነት” ማለት አባላት የፋይናንስ አገልግሎቶችን በጥራትና በተደራሽነት መጠቀም ሲችሉ ነው፡፡

3.16 “የኅብረት ስራ ማህበሩ ዋና ጽ/ቤት” ማለት የኅብረት ስራ ማህበሩ አጠቃላይ ተግባራት የሚመራበት ጽ/ቤት ማለት ነው፡፡

3.17 “የኅብረት ስራ ማህበሩ ቅርጫፍ ጽ/ቤት” ማለት ለኅብረት ስራ ማህበሩ ዋና ጽ/ቤት ተጠሪ ሆኖ በተሰጣቸው ተግባርና ሀላፊነት መሰረት ለአባላት ተደራሽ የፋይናንስ አገልግሎት የሚሰጡ ጽ/ቤቶች ናቸው፡፡

4. **የኅብረት ሥራ ማህበሩ ኃላፊነት**

ኅብረት ሥራ ማህበሩኃላፊነቱ የተወሰነ በመሆኑ ስራውን በሚያከናውኑበት ወቅት ለሚገጥመው ኪሳራ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በእዳ ተጠያቂ አይሆንም፣

5. **ህጋዊ ሰውነት፣**

5.1 ኅብረት ሥራ ማህበር ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ በህግ የሰውነት መብት ይኖረዋል፣ ይኸውም ውል የመዋዋል፣ የመክሰስ፣ የመከሰስ፣ የማበደር፣ የመበደር መብትና ግዴታዎች እንዲሁም በስሙ ንብረት የማፍራት መብት ይኖሩታል፣

5.2 አግባብ ያለው ባለስልጣን መመሪያ መሰረት ኅብረት ሥራ ማህበሩ በየሶስት አመቱ ህጋዊ ሰውነቱን ማሳደስ አለበት፣

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
መዝገብ ቤት
Archive
Ethiopian Cooperative Commission Archive

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Kefeta Youth Primary SACCO Ltd.Liab

6. የኅብረት ሥራ ማህበሩ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዓላማ እና ተግባር

6.1. የኅብረት ሥራ ማኅበሩ ራዕይ

በ2030 ዓ.ም የአባላትን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ያረጋገጠ የኅብረት ስራ ማኅበር ሆኖ ማየት፣

6.2. የኅብረት ሥራ ማኅበሩ ተልዕኮ

ለህብረተሰቡ የፋይናንስ ትምህርትና ስልጠና በመስጠት የፋይናንስ አጠቃቀም ንቃተ ህሊና በማሻሻል አባላትን በስፋት ማፍራት፤የአባላትን ፍላጎት መሰረት በማድረግ የቁጠባ አገልግሎቶችን ማስፋፋትና ቁጠባን ማሰባሰብ፤ የብድር አገልግሎትን በብዛት፣ በጥራት እና በተመጣጣኝዋጋ ለአባላት ማቅረብ፤የአነስተኛ ኢንሹራንስ አገልግሎትን በማስፋፋት ሊደረስ የሚችለውን ጉዳት መቀነስ፤ ተወዳዳሪ የሰው ሀይል በማሟላትና ደረጃውን የጠበቀ ቴክኖሎጅ በመጠቀም የአገልግሎት አሰጣጡን በማዘመን የአባላትን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ።

6.3. የኅብረት ሥራ ማህበሩ አላማ፣

6.3.1. ለህብረተሰቡ የፋይናንስ ትምህርትና ስልጠና በመስጠት የፋይናንስ አጠቃቀም ንቃተ ህሊና በማሻሻል አባላትን በስፋት ለማፍራት፣

6.3.2. የአባላትን ፍላጎት መሰረት ያደረገ የተለያዩየቁጠባ አገልግሎቶች በማስፋፋት ቁጠባን በስፋት ለማሰባሰብ፣

6.3.3. የአባላትን ፍላጎት መሰረት ያደረገ የተለያዩ የብድር አገልግሎቶችንበማስፋፋት የብድር አገልግሎትን በብዛት፣ በጥራት እና በተመጣጣኝ ዋጋ ለአባላት በማቅረብየኢንቨስትመንት አቅም ለማሳደግ፣

6.3.4. የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት ስርዓት በመዘርጋት አባላትን መሰረት ያደረገ የፋይናንስ አገልግሎት በመስጠት የኢንቨስትመንት አቅምንለማጎልበት፣

6.3.5. የአነስተኛ መድን ዋስትና ወይም የተካፋል አገልግሎት በመስጠት በኅብረት ስራ ማህበሩና በአባላት ላይ ሊደርስ የሚችለውን የአደጋ ስጋት ለመቀነስ፣

6.3.6. የፋይናንስ ተቋማት እና ኅብረት ሥራ ማህበሩ የፋይናንስ ትስስር በመፍጠር የሚከሰተውን የፋይናንስ እጥረትና ክምችት ችግርን ለመፍታት፣

6.4. የኅብረት ሥራ ማህበር ተግባራት

6.4.1. ለወጣቱ በፋይናንስ አጠቃቀም ላይ ትምህርትና ስልጠና መስጠት፣

6.4.2. አዳዲስ አባላትን ማፍራት፣

6.4.3. የኅብረት ሥራ ማህበሩ ካፒታል ማሳደግ፣

6.4.4. የቁጠባ አገልግሎቶችን ማስፋፋትና ቁጠባን በስፋት ማሰባሰብ፣

6.4.5. የብድር አገልግሎቶችን ማስፋፋትና ብድርን ለአባላት መስጠትና ማስመለስ፣

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
መዝገብ ቤት
Archive
Ethiopian Cooperative Commission Archive

6.4.6. አባላት ገንዘባቸውን አዋጭነት ባለው ስራ እንዲያውሉ የምክር አገልግሎት መስጠት፣

6.4.7. የአደራ ገንዘብናተዘዋዋሪ ብድሮችን ተረክቦ ማስተዳደር፣

6.4.8. የወለድ አልባ የፋይናንስ አግልገሎት መስጠት፣

6.4.9. የአነስተኛ መድን ዋስትና ወይም ተካፉል አገልግሎት መስጠት፣

6.4.10. ዘመናዊ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት አገልግሎት መስጠት፣

6.4.11. ለአባላት፣ ለአመራር አካላት፣ ቅጥር ሰራተኞች አስፈላጊው ትምህርት፣ ስልጠና መስጠት፣

6.4.12. ዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጂ ስርዓት መዘርጋት የኅብረት ሥራ ማህበሩና የአገልግሎት አሰጣጥ ማዘመን፣

6.4.13. ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረት ማፍራትና ማስተዳደር

6.4.14. ከተለያዩ የፋይናንስ ተቋማትና አጋር አካላት ጋር ትስስር መፍጠር፣

6.4.15. ሌሎች በጠቅላላ ጉባኤ የሚሰጡ ተግባራትን ይፈጽማል፣

7. የኅብረት ስራ ማህበሩ ዋና እና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተግባርና ሀላፊነት

7.1.1. የኅብረት ስራ ማህበሩ ዋና ጽ/ቤት ተግባርና ሀላፊነት

7.1.1.1. የኅብረት ሥራ ማህበሩን ዕቅድ እና በጀት ማዘጋጀትና ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ማከፋፈል፣

7.1.1.2. የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሰው ሀይል መቅጥር፣ ማደራጀትና ማስተዳደር፣

7.1.1.3. የኅብረት ስራ ማህበሩን የሚመራበትን የሂሳብ፣ የሰው ሀብት አስተዳደር፣የቁጠባ፣ የብድር፣አነስተኛ ኢንሹራንስ ፣ ወለድ አልባ፣ የውስጥ አሰራር፣ የጠቅላላ ጉባኤ ተወካይ አወካከል እና የግዥና ንብረት አስተዳደር የአሰራር ስርአቶችን መዘርጋት፣

7.1.1.4. የኅብረት ስራ ማህበሩን የጠቅላላ ጉባኤ ማካሄድ፣

7.1.1.5. የኅብረት ስራ ማህበሩ የአባላት የእጣ ሰርተፊኬት በማሳተም ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ያከፋፍላል፣

7.1.1.6. የኅብረት ስራ ማህበሩን መተዳደሪያ ደንብና ውስጠ ደንብ ማሻሻልና ማፀደቅ፣

7.1.1.7. የኅብረት ስራ ማህበሩን የስራ አመራር፣ ቁጥጥርና ሌሎች ንኡሳን ኮሚቴዎችን ማስመረጥ፣

7.1.1.8. ኅብረት ስራ ማህበሩን በመወከል ውሎችን መፈጸም፣ መክሰስ፣ መበደር፣ ሀብትና ንብረቶችን ማስተዳደር፣

7.1.1.9. ከሌሎች አጋር አካላትና ተቆጣጣሪ ተቋማት ጋር የስራ ግንኙነት ማድረግ፣

7.1.1.10. የኅብረት ስራ ማህበሩን አመታዊ የስራ እንቅስቃሴዎችን ኦዲት ማስደረግ፣

7.1.1.11. የኅብረት ስራ ማህበሩን አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴ ሪፖርቶችን በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል ማቅረብ፣

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
መዝገብ ቤት
Archive
Ethiopian Cooperative Commission Archive

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Kefeto Youth Primary SACCO Ltd/Liab

7.1.1.12. ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን መክፈት፣ ቢሮ መከራየት፣ ማደራጀት፣ መከታተል፣ መመዘን፣ ደረጃ መስጠትናማስተዳደር

7.1.1.13. የኀብረት ስራ ማህበሩን የመረጃ አያያዝ ቴክኖሎጅ መዘርጋትና ማስተዳደር፣

7.1.1.14. ለቅርጫፍ ጽ/ቤቶች ከተሰጠው የብድር ጣሪያ በላይ የሆነ ብድሮችን ማፅደቅ፣

7.1.1.15. የኀብረት ስራ ማህበሩን ፋይናንስ ግብይት ትስስር መፈፀምና ማስተዳደር፣

7.1.1.16. ዋና የብድር ውሎችንና የዋስትና ሰነዶችን ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በማሰባሰብ አደራጅቶ መያዝ፣

7.1.1.17. የኀብረት ስራ ማህበሩን የባንክ ሂሳቦችን መክፈትና ማስተዳደር፣

7.1.1.18. የኀብረት ስራ ማህበሩን የስራ እንቅስቃሴ ማስመዘንና ህጋዊ ሰውነቱን ማሳደስ፣

7.1.1.19. ኀብረት ስራ ማህበሩ የሚያደርጋቸውን የስራ እንቅስቃሴዎች ማስተዋወቅ፣

7.1.1.20. የኀብረት ስራ ማህበሩን ሂሳብ ሰነዶች፣ መዛግብቶች፣ ቅፃቅፆችን ማሳተምና ማሰራጨት፣

7.1.1.21. የኀብረት ስራ ማህበሩን የስራ እንቅስቃሴ የሚገልፁ መረጃዎችን በአግባቡ አደራጅቶ መያዝ፣

7.1.1.22. የኀብረት ስራ ማህበሩን ቋሚ ንብረት ግዥ መፈፀም፣ ለቅርጫፍ ጽ/ቤቶች ማሰራጨት እና ማስተዳደር

7.1.1.23. የኀብረት ስራ ማህበሩን ትርፍ ለአባላት ማከፋፈል፣

7.1.1.24. የኀብረት ስራ ማህበሩን የመጠባበቂያ ተቀማጭ ሂሳብ መክፈትና ማስተዳደር፣

7.1.1.25. የኀብረት ስራ ማህበሩ የሚያደረጋቸው ማህበራዊ ተሳትፎዎችን መለየትና መተግበር

7.1.2. የኀብረት ስራ ማህበሩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተግባርና ሀላፊነት

7.1.2.1. ለአካባቢው ማህበረሰብ በፋይናንስ አገልግሎት አጠቃቀም ላይ ትምህርት፣ ስልጠናና መረጃ መስጠት፣

7.1.2.2. አዳዲስ አባላትን ማፍራትና የእጣና መመዝገቢያ ክፍያ መሰብሰብ፣

7.1.2.3. የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱን መነሻ እቅድ አዘጋጅቶ ለዋና ጽ/ቤት መላክ፣

7.1.2.4. ቁጠባ ማሰባሰብ፣ እጣ መሸጥ እና ከአባላት አረቦን ክፍያ ማሰባሰብ፣

7.1.2.5. የተፈቀደለትን የብድር ጣሪያ መሰረት በማድረግ ለአባላት ብድር መስጠትና ማስመለስ፣

7.1.2.6. የአነስተኛ ኢንሹራንስ ተጠቃሚ አባላት ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን በማጣራት ለዋና ጽ/ቤት መላክና ክፍያ እንዲፈፀም ክትትል ማድረግ፣

7.1.2.7. አባላት ለገዙት እጣ የእጣ ሰርተፊኬት መስጠት፣

7.1.2.8. ከዋና ጽ/ቤት በሚሰጠው ድርሻ መሰረት እጩ የጠቅላላ ጉባኤ ተወካዮችን በማስመልመል መላክ፣

የኢትዮጵያ ኀብረት ሥራ ኮሚሽን
መዝገብ ቤት
Archive
Ethiopian Cooperative Commission Archive

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Kefeta Youth Primary SACCO Ltd.Liab

7.1.2.9. ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የተመደቡ የስራ ማስኪያጃ ወጪዎችን ማስተዳደር፣

7.1.2.10. ለብድር ዋስትና የተያዙ የብድር ውሎችንና የዋስትና ሰነዶችን ዋናውን ቅጅ/ኦሪጅናል/ ለዋና ፅ/ቤት መላክና ቅጅውን አደራጅቶ መያዝ፣

7.1.2.11. የአባላትን የቁጠባ፣ የእጣ፣ የብድር፣ ወለድ ሂሳብ በወቅቱ በማስላት ደብተር ላይ መመዝገብ፣

7.1.2.12. የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱን የስራ እንቅስቃሴ በአግባቡ አደራጅቶ መያዝ፣

7.1.2.13. የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱን የስራ አፈፃፀም ለዋና መ/ቤቱ በወቅቱ መላክ

7.1.2.14. የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱን ሰራተኞችን ማስተዳደር፣

7.1.2.15. ከቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሰራተኞች የገቢ ግብር በመሰብሰብ በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ገቢ ማድረግ፣

7.1.2.16. ከአካባቢው ካሉ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ጋር የስራ ግንኙነት ማድረግ፣

8. የኅብረት ሥራ ማህበሩ መርሆዎች፣ ዕሴቶች እና የስነ ምግባር እሴቶች፣

8.1 የኅብረት ሥራ ማህበሩ መርሆዎች፣

8.1.1. አባልነት በፈቃደኝነትና በፍላጎት ላይ የተመሰረተ እና ለሁሉም ክፍት ማድረግ፣

8.1.2. ዲሞክራሲያዊ አሰራና አመራር ማስፈን፣

8.1.3. አባላት ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማስቻል፣

8.1.4. ራስ አገዝና ራስን በራስ ማስተዳደር፣

8.1.5. ለአባላትና ለአመራር አካላት ለቅጥር ሰራተኞች ተከታታይ ትምህርት ፣ስልጠናና መረጃ መስጠት፣

8.1.6. ከሌሎች አቻ ኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር ኅብረት መፍጠር ፣

8.1.7. በአካባቢ ልማት መሳተፍ፣

8.2. የኅብረት ሥራ እሴቶች፣

8.2.1. ራስን በራስ መርዳት፣

8.2.2. የግል ኃላፊነትን መወጣት፣

8.2.3. የዲሞክራሲ ባህል ማስፋፋት፣

8.2.4. እኩልነት፣

8.2.5. ፍትሃዊነት፣

8.2.6. ወንድማማችነት፣

8.3. የአባላት የስነ-ምግባር ዕሴቶች፣

8.3.1. ታማኝነት፣

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚ...
መዝገብ ቤት
Archive
Ethiopian Cooperative Commission ...chive
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Kefeta Youth Primary SACCO Ltd.Liab

8.3.2. ግልጽነት፣

8.3.3. ተጠያቂነት

8.3.4. አሳታፊነት

8.3.5. ማህበራዊ ኃላፊነት፣

8.3.6. ለሌሎች ማሰብ ናቸው፣

9. አባል ለመሆን የሚያበቁ መስፈርቶችና ለአባልነት ስለሚቀርብ ማመልከቻ፣

9.1. የኅብረትስራማህበራችንሙሉአባልለመሆንቢያንስየሚከተሉትንመስፈርቶቹየሚያሟላ መሆንይጠበቅበታል

9.2. ወጣት የሆነ፣ እድሜው ከ18አመት በላይ የሆነና በኅብረት ሥራ ማህበሩ የስራ ክልል የሚኖር፣

9.3. መተዳደሪያ ደንቡን፣ ውስጠ ደንቡን፣ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ያወጣቸው የተለያዩ መመሪያዎች፣ የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎችን የተቀበለና ግዴታውን ለመወጣት ፈቃደኛ የሆነ፣

9.4. በመተዳደሪያ ደንቡ የተቀመጠውን መመዝገቢያና የአባልነት መነሻ ዕጣ ለመግዛት የተስማማ

9.5. በመተዳደሪያ ደንቡ የተቀመጠውን መነሻ መደበኛ ቁጠባ ለመቆጠብ ፈቃደኛ የሆነ፣

9.6. በህግ ችሎታ ያለውና ተቀባይነት ያገኘ ሆኖ ዝርዝረ ሁኔታዉ በዉስጥ ደንብ የሚገለጽ ይሆናል።

9.7. ማንነቱን የሚገልጽ መታወቂያ ማቅረብ የሚችል፣

9.8. በተመሳሳይሌላኅብረትሥራማህበርአባልያልሆነ፣

10. ለኅብረት ሥራ ማህበር አባልነት ስለሚቀርብ ማመልከቻ፣

10.1. አባል ለመሆን የሚፈልግ ግለሰብ ለዚህ ተግባር የተዘጋጀውን የአባልነት ማመልከቻ ቅጽ ሞልቶናፈርሞ ለኅብረት ሥራ ማህበሩ ቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ ወይም ተወካይያቀርባል፣

10.2. ስራ አስኪያጁ ወይም ተወካዩየቀረበለትን የአባልነት ማመልከቻ መርምሮበ15 ቀናት ውስጥ አባልነት ለጠየቀው ግለሰብአባል እንዲሆን ስለመቀበሉ በጽሁፍ መልስ ይሰጣል፣ ግለሰቡ አስፈላጊውን ፎርማሊቲ አሟልቶ አባል ይሆናል፣

10.3. ስራ አስኪያጁ ወይም ተወካዩአባልነቱን ያልተቀበለከሆነ ያልተቀበለበትን ምክንያት በጽሁፉ ምላሽ ይሰጣል፣

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
መዝገብ ቤት
Archive
Ethiopian Cooperative Commission Archive
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Kelata Youth Primary SACCO

10.4. ስራ አስኪያጁ ወይም ተወካዩ አባል የሆነውን ግለሰብ አባል ስለመሆኑበጠቅላላ ጉባኤ ሪፖርት ያደርጋል

10.5. አመልካቹ በውሳኔው ቅሬታ ካለው አግባብ ላለው ባለስልጣን በጽሁፍ ይግባኝ ሊጠይቅ ይችላል

10.6. በድጋሚ አባል ለመሆን የሚፈልግ አመልካች እንደ አዲስማመልከቻውን ሞልቶ ማቅረብ ይኖርበታል

10.7. የአባልነት ማመልከቻ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ያዘጋጃል፣

11. ስለ አባላት ምዝገባ፣

የኅ/ሥራ ማህበሩ ቅርጫፍ ጽ/ቤትከዚህ በታች በተጠቀሱት ነጥቦች መሰረት የአባላት መዝገብ አዘጋጅቶ መዝግቦ ይይዛል፣

11.1. የአባልነት መለያ ቁጥር

11.2. የአባሉ ስም፣ አድራሻ፣ ስራ፣ እድሜ እናጾታ፣

11.3. አባል የሆነበት ቀን፣ ወር እና ዓ/ም

11.4. የተከፈለ መመዝገቢያና ዕጣ መጠን ፣

11.5. አባልነት ያቋረጠበት ቀን፣ ወርና ዓ/ም

11.6. ያቋረጠበት ምክንያት፣

12. የአባላት መብትና ግዴታ

12.1 የአባላት መብት

12.1.1. ስለ ኅብረት ሥራ ማህበሩ እንቅስቃሴ የሚፈልገውን መረጃ ጠይቆ የማግኘት ፣

12.1.2. በጠቅላላ ጉባኤ ላይ በውክልና የመሳተፍ፣ ሃሳብን በነጻ የመግለጽ፣ ድምጽ የመስጠት፣

12.1.3. አመራሮችን የመምረጥና የማሰናበት፣ እንዲሁም በአመራርነት የመመረጥ፣

12.1.4. ኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚሰጠውን አገልግሎትና ጥቅም የማግኘት፣

12.1.5. ኅብረት ሥራ ማህበሩበሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ማንኛውንም ጥያቄ፣ ቅሬታ፣ አስተያየት ማቅረብና መልስ የማግኘት፣

12.1.6. ጥቅሞቹ ተከብረውለት በጥያቄው መሰረት የመሰናበት፣

12.2. የአባላት ግዴታዎች

በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅና መመሪያ መሰረት እያንዳንዱ አባል የሚከተለውን ግዴታመወጣት አለበት፣

12.2.1. የመመዝገቢያ፣ ዝቅተኛውን የአባልነት የእጣ ዋጋ የመክፈል እና ዝቅተኛውን መደበኛ ቁጠባ በወቅቱ የመቆጠብ፣

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ...
መዝገብ ቤት
Archive
Ethiopian Cooperative Commission ...chive
The Federal Democratic Republic Ethiopia Kofota Youth Primary SACCO Ltd

12.2.2. የኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ፣ የውስጥ አሰራር መመሪያዎች፣ ውስጠ ደንቦችና ውሳኔዎች የማክበር እና የመፈጸም፣

12.2.3. በጠቅላላ ጉባኤ ላይ በውክልና መገኘት፣

12.2.4. የኅብረት ሥራ ማህበሩ ኪሳራ መጋራት፣

12.2.5. የኅብረት ሥራ ማህበር የጋራ ንብረት መንከባከብ፣

12.2.6. አባሉ በገባው ውል መሰረት የወሰደውን ብድር በወቅቱ የመክፈል፣

13. አባልነት ስለመቋረጥ፣

13.1. በአባሉ በፍላጎት ከኅብረት ሥራ ማህበሩ የመወጣት ጥያቄ ካቀረበ፣

13.2. የኅብረት ሥራ ማህበሩ በሚሰጠው የስራ ዘርፍና ኃላፊነት ግዴታውን ባለመወጣት፣

13.3. ኅብረት ሥራ ማህበሩ ሳያሳውቅ የሚፈለግበትን የቁጠባና የእጣ ክፍያ በገባው ውል መሰረት ለ6-(ስድስት) ተከታታይ ጊዜ ሳይከፍል ከቀረ፣

13.4. የኅብረት ሥራ ማህበሩ ንብረቶች ላይ ሆን ብሎ አደጋ ያደረሰ ወይም እንዲደረስ ያደረገ፣

13.5. የኅብረት ሥራ ማህበሩ ንብረት ለግል ጥቅም ያዋለ፣

13.6. የኅብረት ሥራ ማህበሩ ገንዘብ ሆን ብሎ በማጉደል ወይም ለማጉደል ሁኔታዎችን ያመቻቸ፣

13.7. በኅብረት ሥራ ማህበሩ ስም ህገወጥ ተግባራትን የፈጸመ፣

13.8. አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ፣ መተዳዳሪያ ደንብና የአባላትን ውሳኔ ያላከበረና እና ያልፈጸመ፣

13.9. የኅብረት ሥራ ማህበሩ የብድር አስተዳደር መመሪያ በማዛባት ለራስ ጥቅም ሲባል አላስፈላጊ ብድር የወሰደ፣

13.10. የኅብረት ሥራ ማህበሩን የሂሳብ መግለጫዎችሆን ብሎ ያሳሳተ፣

13.11. ኅብረት ሥራ ማህበሩ ሳያሳውቅ በተቀመጠው የብድር መመለሻ ጊዜ ውስጥ መመለስ ያለበትን ብድር እንዲመልስ ተገልጾለት በቂ ምክንያት ሳያቀርብ መመለስ ካልቻለ፣

13.12. አባሉ በሞት ሲለይ፣

13.13. አባሉ በህግ ወይም በፍርድ የታገደ ከሆነ፣

14. የአባልነት ስንብት አፈጻጸም፣

14.1. አባሉ በራሱ ጥያቂ ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ለመውጣት ከፈለገ ከ 15 ቀን በፊት ለቅርንጫፍ ፅ/ቤት በማመልከቻ ማቅረብ ይኖርበታል፣

14.2. በአባሉ ጥያቄ የተደረገ ስንበት በቅርጫፍ ጽ/ቤት ስራ አስኪያጅ ወይም ተወካይ ውሳኔ መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፣

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
መዝገብ ቤት
Archive
Ethiopian Cooperative Commission

14.3. አንድ አባል ጥፋተኛ መሆኑ በቅርጫፍ ጽ/ቤት ከተረጋገጠ ለስራ አመራር ኮሚቴ ቀርቦ ውሳኔ ይሰጥበታል፣

14.4. በስራ አመራር ኮሚቴ እንዲሰናበት ውሳኔ የተላለፈበት አባል በ 10(አስር) ቀናት ውስጥ የስንብት ደብዳቤ በቅርጫፍ ጽ/ቤት በኩል እንዲደርሰው ይደረጋል፣

14.5. ከኅብረት ሥራ ማህበሩ የተሰናበተ አባል እዳ እንደሌለበት ከተረጋገጠ ጥቅሙና ድርሻው ይጠበቅለታል፣ ይሁን እንጂ ጥቅሙ የሚጠበቅለት ኅብረት ሥራ ማህበሩ ኦዲት ከተደረገና ኪሳራ እንደሌለበት ከተረጋገጠ በኋላ ነው፣

14.6. አንድ አባል በማንኛውም ምክንያት ከኅብረት ሥራ ማህበሩ መልቀቅ በሚፈልግበት ጊዜ እዳ እንዳለበት ሲታወቅ ካለው ድርሻ ወይም ጥቅሞች ለእዳ ተቻችሎ የሚቀረው ገንዘብ ይከፈለዋል፣

14.7. በራሱ ፈቃድ ከአባልነት የተሰናበተ አባል ወደ ኅብረት ሥራ ማህበሩ እንደገና አባል ለመሆን ጥያቄ ካቀረበ የሚጠበቅበትን መመዝገቢያ ክፍያ በመክፍልና እጣ በመግዛት አባል መሆን ይችላል፣

14.8. ግዴታውን ባለመወጣቱ ከአባልነት የተሰናበተ አባል ጥያቄውን ካቀረበ በአንድ በጀት አመት በኋላ ስራ አመራር ኮሚቴ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት መመለስ ይቻላል፣

14.9. ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ጋር በተያያዘ በወንጀል ወይም በተለያዩ ጥፋቶች ከአባልነት የተሰናበተ አባል እንደገና አባል ለመሆን የሚችለው ከተሰናበተበት ዓመት ጀምሮ ከአምስት አመት በኋላ በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሰረት ወደ አባልነት መመለስ ይችላል፣

15. **የመመዝገቢያ ክፍያ እና የዕጣ ክፍያ**

15.1 የመመዝገቢያ ክፍያ

15.1.1 ማህበሩ የመመዝገቢያ ክፍያ ያስከፍላል ሆኖም ያከፋፈል ሁኔታዉና የክፍያ መጠኑ በዉስጥ ደንብ ይገለፃል።

15.1.2. ለመመዝገቢያ የተከፈለ ገንዘብ ለከፋዩ ተመላሽ አይሆንም፣ ጥቅምም አያስገኝም፣

15.1.3. የመመዝገቢያ ክፍያ ለኅብረት ሥራ ማህበሩ ስራ ማስኬጃነት ይውላል፣

15.1.4. አንድ አባል ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ከተሰናበተ በኋላ እንደገና አባል እንዲሆን ከተፈቀደለት እንደ አዲስ አባል የመመዝገቢያ ክፍያ ይከፍላል፣

15.1. የእጣ ክፍያ

15.1.1.የአንድ የእጣ ዋጋ ብር 250(ሁለት መቶ ሀምሳ ብር)ሆኖየኅብረት ሥራ ማህበሩ አባል ለመሆን ቢያንስ 4(አራት) እጣዎች መግዛት ይኖርበታል፣

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ... መዝገብ ቤት Archive Ethiopian Cooperative Commission Archive

15.1.2. አንድ አባል እንዲሸጥ ከተወሰነው ጠቅላላ የእጣ መጠን ውስጥ 10 በመቶ በላይ ድርሻ አይኖረውም፣

15.1.3. ኅብረት ስራ ማህበሩ ለሽያጭ 70,000እጣዎች ያዘጋጀ ሲሆን ኅብረት ስራ ማህበሩ ሲቋቋም 1/5ኛው የሚሸጥ ሲሆን ቀሪ እጣዎችን በአራት አመት ግዜ ውስጥ ሸጦ መጨረስ አለበት፣ከአራት አመት በፊት ተሸጦ ካለቀ ተጨማሪ ዕጣዎችን ለመሸጥ በውሥጠ ደንብ አስወስኖ ተግባራዊ ማድረግ ይችላል፣

15.1.4. ኅብረት ሥራ ማህበሩ የተለያዩ ኢንቨስትመንት ስራዎችን ለማከናወን ሲፈልግ እጣዎችን በጠቅላላ ጉባኤ ወስኖ መሸጥ ይችላል፣

15.1.5. እያንዳንዱ አባል በየጊዜው ከመደበኛ ቁጠባ እድገት ጋር የተጣጣመ የእጣ መጠን እንዲኖረው ለማድረግየቁጠባና እጣ ምጥጥን 1 ለ 4 ይሆናል፣

15.1.6. የአባላት እጣግዥ ከመደበኛ ቁጠባ ጋር አብሮ የሚሰበሰብ ሆኖቁጠባውና እጣውተለይቶ መመዝገብ ይኖርበታል፣

15.1.7. አባል እንዲሆን የተፈቀደለት አመልካች ከተፈቀደለት ቀን አንስቶ በ 2(ሁለት ወራት) ጊዜ ውስጥ አባል ለመሆን የሚያስችለውን የመነሻ እጣ መጠንን ከፍሎ ማጠናቀቅ አለበት፣

15.1.8. ዕጣ ለአባል ተመላሽ የሚሆነው አባልነት ሲቋረጥ ብቻ ይሆናል፣

15.1.9. የኅብረት ስራ ማህበሩ ዕጣ ለገዛ አባል የዕጣ ሰርተፍኬት አዘጋጅቶ ይሰጣል፣

15.1.10. የኅብረት ስራ ማህበሩ ካፒታል የመደበኛ ቁጠባ ደህንነት የሚጠብቅ በመሆኑ ገቢ በማያስገኙና የረጅም ጊዜ ኢንቨስትምነት ላይ አይውልም፣

16. ስለ ድምጽ አሰጣጥ፣

16.1. ማንኛውም አባል ኅብረት ሥራ ማህበሩ ውስጥ ያለው እጣ መጠን ግምት ውስጥ ሳይገባ የሚሰጠው ድምጽ አንድ ብቻ ይሆናል፣

16.2. መደበኛና አስቸኳይ የጠቅላላ ጉባኤ እንዲሁም የኮሚቴዎች ስብሰባዎች ላይ የሚወሰኑ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ መሆን አለበት፣

16.3. በኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚጸድቅ ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ 50+1(ሀምሳ ሲደመር አንድ) ነው፣ ሆኖም ግን ልዩ ውሳኔ የሚያስፈልጉ ጉዳዮች 2/3(በሁለት ሶስተኛ) ድምጽ መጽደቅ ይኖርበታል፣

16.4. በድምጽ አሰጣጥ ወቅት የድምጽ አሰጣጡ እኩል የተከፈለ ከሆነ ሰብሳቢው ያለበት ድምጽ የሚጸና ይሆናል፣

17. የ[illegible]፣

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚ. መዝገብ ቤት Archive Ethiopian Cooperative Commission Archive
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Kefeta Youth Primary SACCO Ltd.Liab

17.1. ኅብረት ሥራ ማህበሩን የሚመሩ ኮሚቴዎች የሚሰየሙት በምርጫ መሆን አለበት፣

17.2. የኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ተወካዮች የስራ ጊዜያቸውን ያጠናቀቁ ወይም የጎደሉ የኮሚቴ አባላትን ከአባላት መካከል መርጦመተካት አለበት፣

17.3. የስራ አመራር ኮሚቴና የቁጥጥር ኮሚቴ ምርጫን የሚያከናውኑ 3(ሶስት) አባላት ያሉት አስመራጭ ኮሚቴ ምርጫ ከመደረጉ በፊት በጠቅላላ ጉባኤ ተወካይ ይመረጣሉ፣

17.4. በጠቅላላ ጉባኤ እለት ኅብረት ሥራ ማህበሩንሲመሩ የነበሩ አመራር አካላት የምርጫውን ስነስርዓት ለሚያከናውኑትአስመራጭ ኮሚቴዎች ስልጣናቸውን ማስረከብ አለባቸው፣

17.5. ለስራ አመራር ኮሚቴ፣ ለቁጥጥር ኮሚቴ እና ለንዑሳን ኮሚቴ አባልነት ምርጫ የሚቀርቡ እጩዎች ለየኮሚቴዎቹ በሚያስፈልጉ አባላት ብዛት ላይ 2(ሁለት) እጩዎችን በመጨመር እንዲወዳደሩ ይደርጋል፣

17.6. በየኮሚቴዎቹ በእጩነት ቀርበው በድምጽ ብልጫ የወደቁ እጮዎች በተጠባባቂነት ተይዘው ከከኮሚቴ አባላት ውስጥ በተለያየ ምክንያቶች ሲጎሉ የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ሳያስፈልግ በቅድም ተከተላቸው መሰረት በቀጥታ የሚተኩ ይሆናል፣

17.7. የድምጽ አሰጣጥ ስርዓቱ በቀጥታ ይሆናል፣

17.8. የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት ለስራ አመራር ኮሚቴና ለቁጥጥር ኮሚቴ አባልነት በእጩነት ሊቀርቡ አይችሉም፣

17.9. በጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡ የስራ አመራር ኮሚቴና ቁጥጥር ኮሚቴ አባላት ምርጫው እንደተደረገ የስራ ክፍፍል በማድረግ ወዲያውኑ ለጠቅላላ ጉባኤ የስራ ድርሻቸውን ያሳውቃሉ፣

17.10. የአስመራጭ ኮሚቴ 30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በተሻሩና በተመረጡ የስራ አመራር ኮሚቴና የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት መካከል የስራ ርክክብ እንዲፈጸም ያደርጋል፣

17.11. ነባሩ የስራ አመራር ኮሚቴ እና የቁጥጥር ኮሚቴ ለተተኪው አዲስ አመራር አባላት ስራውን የማለማመድና የምክር አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለባቸው፣

17.12. የኅበረት ስራ ማህበሩ ኮሚቴዎች የስራ ግዜ ሶስት አመት ሆኖ የመተካካት መርህን ተግባራዊ ለማድረግ በየአመቱ ከኮሚቴ አባላት ውስጥ 1/3 ኛው አዲስ አባላት መተካት ይኖርበታል፣ሆኖም አንድ ኮሚቴ አባል ከስድስት አመት በላይ መቆየት አይችልም፣

17.13. የኮሚቴ አባላት የዲሲፕሊን ግድፈት ሲገኝባቸው በየትኛውም ግዜ በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ይባረራሉ፣

18. ኅብረት ሥራ ማህበሩ ድርጅታዊ መዋቅር፣

18.1. ጠቅላላ ጉባኤ

18.2. የሥራ አመራር ኮሚቴ

18.3. የቁጥጥር ኮሚቴ

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚ... መዝገብ ቤት Archive Ethiopian Cooperative Commission Archive

18.4. ሌሎች ንዑሳን ኮሚቴዎች

The Federal Democratic Republic
Ethiopia Kefeta Youth
Primary SACCO Ltd.

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
መዝገብ ቤት
Archive
Ethiopian Cooperative Commission Archive

የኅብረት ስራ ማህበሩ ድርጅታዊ መዋቅር



19. የጠቅላላ ጉባኤ አቋም፣ስልጣንና ተግባር

19.1. የጠቅላላ ጉባኤ አቋም፣

19.1.1. ማንኛው የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባል በውክልና በጠቅላላ ጉባኤ ላይ በአካል ተገኝቶ ድምጽ መስጠት ይኖርበታል፣

19.1.2. የኅብረት ስራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ተወካዮች ቁጥር 50 ሆኖ በሂደት አባላት ቁጥር ሲጨመር ይሻሻላል

19.1.3. የጠቅላላ ጉባኤ ተወካዮች የሚወከሉት ከየኅብረት ስራ ማህበሩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ባላቸው የአባላት ብዛት መሰረት የሚወሰን ሆኖ ዝርዝር አወካከሉ በውስጠ ደንብ የሚገለጽ ይሆናል፣

19.1.4. ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከሚወከሉ የጠቅላላ ጉባኤ ተወካዮች ውስጥ ቢያንስ 30 ከመቶ ሴቶች መሆን አለባቸው፣

19.1.5. የኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በኅብረት ሥራ ማህበሩ በማንኛውም ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪ አካል ይሆናል፣

19.1.6. የጠቅላላ ጉባኤው ተወካይ አባላት በየሶስት አመቱ ሊቀየሩ ይችላል፣ ሆኖም ከሁለት ጊዜ በላይ መመረጥ አይችሉም፣

19.1.7. ከጠቅላላ ጉባኤ ተወካይነት የተነሳ አባል የሚተካው ከተወከለበት ከቅርንጫፍ ጽ/ቤት መሆን አለበት

19.1.8. የጠቅላላ ጉባኤ አባል ወይም ተወካይ አንድ ድምጽ ብቻ ይኖረዋል፣

19.2. ለጠቅላላ ጉባኤ ተወካይነት የሚያበቁ መስፈርቶች፣

19.2.1. በፍርድ ወይም በህግ የመስራት መብቱ ያልተከለከለ፣

19.2.2. በፍርድ ቤት የወንጀል ክስ ውሳኔ ያልተሰጠበት፣

19.2.3. ሰዎችን ለመርዳት ጽኑ ፍላጎት እና ተቆርቋሪነት ያለው፣

19.2.4. በአመራር ብቃቱና ችሎታው በአባላትየተመሰከረለት፣

19.2.5. የትምህርት ደረጃው ከ10ኛ ክፍልእና ከዚያ በላይ የሆነ፣

19.2.6. በኅብረት ሥራ ማህበሩ አመራርነት ተመርጦ ለመስራት ሙሉ ፈቃደኛ የሆነ፣

19.2.7. የኅብረት ስራ ማህበሩ ቅጥር ሰራተኛ ያልሆነ፣

19.3. የጠቅላላ ጉባኤ ስልጣንና ተግባር፣

19.3.1. ኅብረት ሥራ ማህበሩንየሚመሩ የስራ አመራር ኮሚቴና የቁጥጥር ኮሚቴን ይመርጣል፣ ይሽራል

19.3.2. የኅብረት ሥራ ማህበሩ አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴዎች የሚገልጽ በስራ አመራር ኮሚቴ የቀረበውን ሪፖርት ያዳምጣል፣ ውሳኔ ያስተላልፋል፣

19.3.3. የኅብረት ሥራ ማህበሩንኦዲት ሪፖርት ያዳምጣል፣ ያጸድቃል፣

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
Ethiopian Cooperative Commission Archive
መዝገብ ቤት
Archive
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Kefeta Youth Primary SACCO Ltd.

19.3.4.የኅብረት ሥራ ማህበሩ ስራ ለማስፋት የሚረዳ የገንዘብ መጠን ከአበዳሪ ድርጅቶች መበደር እንዲችሉ ለስራ አመራር ኮሚቴ የብድር ጣሪያ መጠን ይወስናል፣

19.3.5.በጥፋት እና ግዴታውን ባለመወጣት ከአባልነት የተሰናበት በድጋሚ የአባልነት ጥያቄ ካቀረበ ውሳኔ ይሰጣል፣

19.3.6.የኅብረት ሥራ ማህበሩንመተዳደሪያ ደንብ ያሻሽላል፣ የውስጥ አሰራር ደንቦችንና መመሪያዎችን እንዲዘጋጁ ያዛል፣ ያሻሽል፣ ያጸድቃል፣ አፈጻጸማቸውን ይገመግማል፣

19.3.7.የአመራሩ ስነምግባር ደንብ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ያጸድቃል፣ አፈጻጸሙን ይገመግማል፣

19.3.8.የወለድ አልባ የፋይናንስ አሰራር ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ውስጠ ደንብ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ አፈጻጸሙን ይገመግማል፣

19.3.9.የእጣ ዋጋን፣ የሚሸጥ የእጣ ብዛት እና ዝቅተኛ የመደበኛ ቁጠባ መጠንን ይወስናል፣

19.3.10. እንደ አስፈላጊነቱ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሂሳብ ሊመረምር የሚችል የውጭ ኦዲተር አግባብ ባለው ባለስልጣንን በማስፈቀድ ይሰይማል፣

19.3.11. በኅብረት ሥራ ማህበሩ እና በአመራሩ እንዲሁም በአባሉ እና በቅጥር ሰራተኞች መካከል ለሚነሳው አለመግባባት መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፣

19.3.12. የአነስተኛ መድን ዋስትና ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ውሳኔዎችን ያስተላልፋል፣ አፈጻጸሙን ይገመግማል፣ በየጊዜው የአረቦን ክፍያ መጠንን ይወስናል፣

19.3.13. የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሰው ሀይል አስተዳደር መመሪያንያፀድቃል፣

19.3.14. በኅብረት ሥራ ማህበሩ መዋቅራዊ አደረጃጀት እና የሰው ሀይል ብዛትና የደመወዝ መጠን ላይ ውሳኔ ያስተላልፋል፣

19.3.15. የኅብረት ሥራ ማህበሩን የተጣራ ትርፍ ክፍፍል ድልድል ይወስናል፣

19.3.16. በቁጥጥር ኮሚቴ የሚቀርብለትን ሪፖርት ገምግሞ ውሳኔ ይሰጣል፣

19.3.17. የኅብረት ሥራ ማህበሩንእቅድና በጀት ገምግሞ ውሳኔ ያሳልፋል፣ አፈጻጸሙን በሚቀርብለት ሪፖርት መሰረት ይገመግማል፣

19.3.18. የፋይናንስ አሰራር መመሪያ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ያጸድቃል፣ አፈጻጸሙን ይገመግማል፣

19.3.19. የኅብረት ሥራ ማህበሩ የባንክ ሂሳብ በጣምራ የሚያንቀሳቀሱ አመራሮችን ይሰይማል፣

19.3.20. የኅብረት ሥራ ማህበሩ ከሌላ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ጋር እንዲዋሃድ ወይም የኅብረት ሥራ ማህበሩ እንዲከፈል እንዲሁም የፌደሬሽንና የሊግ አባል እንዲሆን ይወስናል፣

19.3.21. ሌሎች በስራ አመራር ኮሚቴ ተጠንተው የቀረቡ አዳዲስ ስራዎችና አገልግሎቶችን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፣

19.3.22. ከየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚወከሉ የጠቅላላ ጉባኤ ተወካዮች የቅርንጫፍ ጽ/ቤታቸውን የስራ አፈፃፀም መከታተል፣ መደገፍ እና መገምገም አለባቸው፣

20. የስራ አመራር ኮሚቴ አመሰራረት፣ስልጣንና ተግባር

21.1 የስራ አመራር ኮሚቴ አመሰራረት፣

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
መዝገብ ቤት
Archive
Ethiopian Cooperative Commission Archive
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Kefeta Youth Primary SACCO Ltd.Liab

21.1.1 የሥራ አመራር ኮሚቴ ተጠሪነቱለጠቅላላ ጉባኤ ይሆናል፤

21.1.2 የስራ አመራር ኮሚቴ ከኀብረት ሥራ ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ አባላት መካከል የተመረጡ ሆነው ቁጥራቸው9 አባላት ይኖሩታል፣

21.1.3 የስራ አመራር ኮሚቴ ሊቀመንበር፣ም/ሊቀመንበር፣ጸሀፊና ሌሎች አባላት ይኖረዋል፣

21.1.4 በጠቅላላ ጉባኤ ውስጥ ካሉ ሴት አባላት መካከል በሥራ አመራር ኮሚቴ አባልነት ከሚመረጡት ውስጥ ቢያንስ 2የሚሆኑት ሴቶች መሆን አለባቸው፡፡

21.1.5 በስራ አመራር ኮሚቴ ውስጥ የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት መስጠት እንዲቻል ሸሪዓን የሚያውቅ አባልይኖራል፣

21.1.6 የእያንዳንዱ የስራ አመራር ኮሚቴ አባል ምርጫ ብቃትንና ችሎታን መሰረት ያደረገ ይሆናል፣

21.1.7 የስራ አመራር ኮሚቴ አባላት የስራ ዘመን በአንድ ምርጫ ጊዜ 3 (ሶስት) አመት ይሆናል፣

21.1.8 የስራ አመራር ኮሚቴ አባላት የስራ ዘመን ከሁለት ጊዜ በላይ ሊሆን አይችልም፣

21.1.9 አንድ የስራ አመራር ኮሚቴ አባል የስራ ጊዜውን ጨርሶ ከወረደ በኂላ በድጋሚ መመረጥ የሚችለው ከሶስት አመት በኂላ ይሆናል፣

21.1.10 የስራ አመራር ኮሚቴ አባል በተመረጠበት የስራ ዘመን ውስጥ ጥፋት አጥፍቶ ከተገኘ ወይም በአባላቱ አመኔታ ካጣወይም መስራት ካልቻለ ወይም የኀብረት ሥራ ማህበሩን‌እንቅስቃሴ ካዳከመ ወይም የገንዘብ ወይም የንብረት ጉድለት/ ብክነት ካደረሰ በማንኛውም ጊዜ በጠቅላላ ጉባኤ ሊሻር ይችላል፣

የኀብረት ሥራ ማህበር የስራ አመራር ኮሚቴ አባል ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ከደረሰበትና በገዛ ፈቃዱ ለመልቀቅ ከፈለገ የስራ አመራር ኮሚቴ መደበኛው ስብሰባ ከመካሄዱ ከ 5 ቀን በፊት በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፣

21.1.11 የኀብረት ሥራ ማህበር ሊቀመንበር የአገልግሎት ጊዜውን ሳይጨርስ በገዛ ፈቃዱ አባልነቱን ቢተው ከስራ አመራር ኮሚቴ አባላት መካከል መርጦ እስከ ቀጣይ ጠቅላላ ጉባኤ ድረስ መተካት ይችላል፣

21.1.12 የኀብረት ሥራ ማህበር የስራ አመራር ኮሚቴ ቋሚ መደበኛ ስብሰባበአካል በመገኘት እና በቨርችዋል ሚቲንግ የሚካሄድ ሲሆን፣ የስብሰባው ቀን በውስጠ ደንብ የሚጠቀስ ይሆናል፣

21.1.13 ከኀብረት ሥራ ማህበርስራ አመራር ኮሚቴ አባላት ውስጥ ሂሳብ የሚያንቀሳቅሱ አመራሮች በማናቸውም ሁኔታ ስራቸውን ሲለቁ በስራ በነበሩበት ወቅት ሲሰሩበት የነበረውን ማንኛወንም ዶክመንት የማስመርምር ግዴታ አለባቸው፣

21.1.14 በማንኛውም ጊዜ የሚደረግ መደበኛ የስራ አመራር ኮሚቴ ስብሰባ ከግማሽ በላይ የሆኑ አባላት ከተገኙ ስብሰባው ሊካሄድ ይችላል፣

የኢትዮጵያ ኀብረት ሥራ ኮሚ.
መዝገብ ቤት
Archive
Ethiopian Cooperative Commission Archive

The Federal Democratic Republic Ethiopia Kefeta Youth Primary SACCO Ltd.Lijib

21.1.15 የኅብረት ሥራ ማህበር የስራ አመራር ኮሚቴ በአዋጅ፣ በመተዳደሪያ ደንብ፣ በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ከተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት ውጭ በሚሰሩት ስራ ምክንያት በኅ/ሥራ ማኅበሩ ላይ በሚደርሰው ኪሳራ ወይም ጥፋት ወይም ጉድለት በጋራ ወይም በግል ተጠያቂ ይሆናሉ፣

21.2. ለኮሚቴ አመራርነት የሚያበቁ መስፈርቶች፣

21.2.1. በፍርድ ወይም በህግ የመስራት መብቱ ያልተከለከለ፣

21.2.2. የኅብረት ሥራ ማህበሩ አመራር አባል ሆኖ የገንዘብ ማባከን፣ ንብረት የማጥፋት እና ሌሎች ኃላፊነት የጎደለው ተግባር ያልፈጸመና ከዚህ ተመሳሳይ ደረጃና ክብደት ያለው ድርጊት ያልፈጸመ፣

21.2.3. በፍርድ ቤት የወንጀል ክስ ውሳኔ ያልተሰጠበት፣

21.2.4. ተደራራቢ የስራ ኃላፊነት የሌለበት፣

21.2.5. ሰዎችን ለመርዳት ጽኑ ፍላጎት እና ተቆርቋሪነት ያለው፣

21.2.6. ከዚህ በፊት በአመራር ብቃቱና ችሎታው በአካባቢው የተመሰከረለት፣

21.2.7. የትምህርት ደረጃው 10+3 ወይም 12+2 እና ከዚያ በላይ የሆነ፣

21.2.8. በኅብረት ሥራ ማህበሩ አመራርነት ተመርጦ ለመስራት ሙሉ ፈቃደኛ የሆነ፣

21.2.9. የሸሪዓ ህግን ጠንቅቆ የሚያውቅ፣

21.2.10. የኅብረት ስራ ማህበሩ ቅጥር ሰራተኛ ያልሆነ፣

21.3. የስራ አመራር ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር፣

21.3.1. የኅብረት ሥራ ማህበሩን ሀብትና እዳ መግለጫ፣ እቅድና በጀት በጠቅላላ ጉባኤ በማቅረብ ያጸድቃል፤

21.3.2. የኅብረት ሥራ ማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ፣ውስጠ ደንቦችን እና የአሰራር መመሪያዎችንእንዲዘጋጅ፣ እንዲሻሻል በማድረግ በጠቅላላ ጉባኤ ያጸድቃል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣

21.3.3. ግዥን እና ሽያጭን መሰረት ያደረጉ ብድሮች ተግባራዊ እንዲሆኑ አስፈላጊ የሆኑ አሰራሮችን ተግባራዊ ያደርጋል፣ አፈጻጸሙን ክትትል ያደርጋል፣

21.3.4. የኅብረት ሥራ ማህበሩመረጃና የሂሳብ አያያዝ ዘመናዊና በቴክኖሎጅ የተደገፈእንዲሆን ያደርጋል፣

21.3.5. አመታዊ የስራ ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፣ አዳዲስ የቁጠባ፣ ብድርና ሌሎች የፋይናንስአገልግሎት አሰራሮችን እንዲቀረፁ ያደርገል፤ ለጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ ያስወስናል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣

21.3.6. የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት መስጠት የሚያስችሉ አሰራሮችን ይቀይሳል፣ በሰውኃይል፣ በአሰራር እና በቁሳቁስ ያደራጃል፣ አገልግሎት አሰጣጡ ሸሪዓን የተከተለ መሆኑን ያረጋግጣል፣

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን መዝገብ ቤት Archive Ethiopian Cooperative Commission Archive

The federal Democratic Republic of Ethiopia Kefeta Youth Primary SACCO Ltd.Liab

21.3.7. የገንዘብ እጥረት ሲያጋጥመው እስከተፈቀደለት የብድር ጣሪያ ድረስ ከፋይናንስ ተቋማት ብድር ይበደራል፣ በወቅቱ እንዲመለስ ያደርጋል፣

21.3.8. የኅብረት ሥራ ማህበሩን የሰው ሀይል አስተዳደር መመሪያ በማዘጋጀት በጠቅላላ ጉባኤ ያጸድቃል፣ የኅ/ሥራ ማኅበሩን አደረጃጀት መዋቅር እና የሰው ሀይል ብዛት እንዲሁም የክፍያ ሁኔታ ያዘጋጃል፣ በየጊዜው ወቅቱ በሚጠይቀው ሁኔታ ያሻሽላል፣ የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ሲያገኝ ተግባራዊ ያደርጋል፣

21.3.9. የአነስተኛ የመድን ዋስትና ወይም ተካፋልን አሰራር በኅብረት ሥራ ማህበሩ ውስጥ ተግባራዊ ያደርጋል ለዚህ የሚሆን መመሪያ ያዘጋጃል፣ በጠቅላላ ጉባኤ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፣

21.3.10. የኅብረት ሥራ ማህበሩ ስብሰባዎች ቃለ ጉባኤ በጽሁፍ ይይዛል፣ መደበኛ እና አስቸኳይ ስብሰባዎችን ይጠራል፣ ስብሰባዎችን ይመራል፣

21.3.11. ግዴታውን ባለመወጣት እና በጥፋት የሚሰናበት አባል ውሳኔ ይሰጣል፣

21.3.12. በማንኛውም ጊዜ ኅብረት ሥራ ማህበሩን በሚመለከቱ ጉዳዮች ወክሎ ይቆማል፣ ውሎችን ይዋዋላል፣

21.3.13. የማይመለስ ብድርን በመለየትና መመለስ የማይቻል መሆኑን በማረጋገጥ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፣

21.3.14. የኅብረት ሥራ ማህበሩ የስራ አመራር ኮሚቴ አባል ጥፋት አጥፍቶ ሲገኝ ለጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ እንዲሰጥበት ያቀርባል፣

21.3.15. የተሻሻለ መተዳደሪያ ደንብ፣የብድር አስተዳደር፣ የቁጠባ አስተዳደር፣ አነስተኛ ኢንሹራንስ መመሪያና ውሰጠ ደንብእንዲመዘገብ አግባብ ላለው ባለስልጣን በማቅረብ ያስመዘግባል፣

21.3.16. የኅብረት ስራ ማህበሩን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን መከታተልና መደገፍ፣

21.4. የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሊቀመንበር ስልጣንና ተግባራት

21.4.1. የኅብረት ሥራ ማህበሩየጠቅላላ ጉባኤውንና የስራ አመራር ኮሚቴ ስብሰባ ይመራል፣

21.4.2. በማንኛውም ጉዳይ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ወክሎ ይከሳል፣ ይከሰሳል፣ ውሎችን ይዋዋላል፣

21.4.3. ለስራ አስኪያጅ ከተፈቀደው ጣሪያ በላይ የሆኑ የኅብረት ሥራ ማህበሩንሂሳብ ያንቀሳቅሳል፣ ሂሳብ ያጸድቃል፣

21.4.4. የኅብረት ሥራ ማህበሩንስራ አስኪያጅ ይቀጥራል፣ ይገመግማል እና ይቆጣጣራል፣ ከስራ በማገድ ለስራ አመራር ኮሚቴ ለውሳኔ ያቀርባል፣

21.4.5. ፍትሃዊ የሰራተኞች አስተዳደር ስርዓት እንዲኖር ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ያደርጋል በስራ አስኪያጅና በቅጥር ሰራተኞች መካከል ያለውን አለመግባባት በሰው ኃይል አስተዳደር መመሪያ መሰረት ይፈታል

21.4.6. ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ የኅብረት ስራ ማህበሩን ስራዎችን ያከናውናል፣

21.5 ምክትል ሊ/መንበር

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
መዝገብ ቤት
Archive
Ethiopian Cooperative Commission Archive
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Kefeta Youth Primary SACCO Ltd.Liab

ሊቀ መንበር በማይኖርበት ግዜ የሊቀ መንበሩን ሥራ ተክቶ ይሰራል

21.6 **የኅብረት ሥራ ማህበሩፀሐፊ**

የኅብረት ሥራ ማህበሩፀሐፊ በጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጥ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናወናል፡፡

21.6.1 የጠቅላላ ጉባኤ እና የስራ አመራር ኮሚቴ ቃለ ጉባኤዎችን ይይዛል፣

21.6.2 ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ሊቀመንበር ጋር በመመካከር የስብሰባ አጀንዳ ያዘጋጃል፣ ከሌሎች ኮሚቴዎች አጀንዳዎችን ያሰባስባል፣

21.6.3 የስብሰባ ጥሪዎችንና አጀንዳዎች ለአባላት ይልካል፣ ለአባሉ ጥሪው መድረሱን ያረጋግጣል፣

21.6.4 ከስራ አመራር ኮሚቴው የሚሰጡትን ተጨማሪ ስራዎች ያከናውናል፣

22. የቁጥጥር ኮሚቴ አቋም፣ስልጣንና ተግባር

22.1. የቁጥጥር ኮሚቴ አቋም

22.1.1 የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት ብዛት 5(አምስት)ሆኖ በጠቅላላ ጉባኤ ይመረጣሉ፣ከእነዚህ መካከል ቢያንስ አንዷ ሴት መሆን አለባት፡፡

22.1.2 የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት የአገልግሎት ዘመን ሶስት አመት ነው፣

22.1.3 የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት ለተከታታይ ከሁለት ጊዜ በላይ መመረጥ አይችሉም፣ ሆኖም በድጋሚ መመረጥ የሚቻለው ከሶስትየኅብረት ሥራ ማህበሩበጀት አመት በኋላ ይሆናል፣

22.1.4 የቁጥጥር ኮሚቴ ሰብሳቢ፣ም/ሰብሳቢ፣ ጸሀፊና አባል ይኖሩታል፣

22.1.5 የቁጥጥር ኮሚቴተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤ ነው፣

22.1.6 የቁጥጥር ኮሚቴ ሰብሳቢ ስራውን በራሱ ፈቃድ ቢያቆም ከኮሚቴ አባላት መካከል አንዱ ተክቶ ይሰራል

22.1.7 ከሁለተኛው ምርጫ አመት ጀምሮ አንድ ሶስተኛው የሆነው የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት በአዲስ ተመራጭ አባል በየጊዜውመተካካት አለበት፣

22.2. የቁጥጥር ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር፣

22.2.1.የቁጥጥር ኮሚቴ በማንኛውም ጊዜ የኅብረት ሥራ ማህበሩን አሰራርና የተለያዩ የሂሳብ ሰነዶችና መዛግብቶችን ይመረምራል፣ ይቆጣጠራል፣

22.2.2.የኅብረት ሥራ ማህበሩየቁጠባና ብድር አሰራር በመተዳደሪያ ደንብ፣በቁጠባና ብድር አስተዳደር መመሪያ መሰረት መከናወኑን ያረጋግጣል፣

22.2.3.የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት በአግባቡ እየተሰጠ ስለመሆኑ ያረጋግጣል፣

22.2.4.የኅብረት ሥራ ማህበሩየሰው ሀይል አመራሩ በሰው ሀይል አስተዳደር መመሪያ መሰረት እየተከናወነ ስለመሆኑ ያረጋግጣል፣

22.2.5.የውስጥ ቁጥጥር አሰራርን ተግባራዊ ያደርጋል፣ ለስራው የሚያስፈልገውን የሰው ሀይልና በጀት በጠቅላላ ጉባኤ አስወስኖ ተግባራዊ ያደርጋል፣

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
መዝገብ ቤት
Archive
Ethiopian Cooperative Commission Archive
The Federal Democratic Republic Ethiopia Kefeta Youth Primary SACCO Ltd.Liab

22.2.6. የፋይናንስ አፈጻጸም መለኪያዎች ተግባራዊ እንዲሆን ከስራ አመራር ኮሚቴ ጋር በመሆን ይሰራል፣የኅብረት ሥራ ማህበሩያለበትን ገምግሞ ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፣

22.2.7. ከስራ አመራር ኮሚቴ ጋር በመሆን አመታዊ የሂሳብ ምርመራ እንዲደረግ ያደርጋል፣ የኦዲት ግኝቶችና የተሰጡ አስተያየቶች ስለመስተካከላቸው ክትትልያደርጋል፣

22.2.8. የቁጥጥር ኮሚቴ ሰብሳቢው በስራ አመራር ኮሚቴ ስብሰባ ላይ በድምጽ አልባነት ይገኛል፣ የስራ አመራር ኮሚቴ ስብሰባ ህግን በተከተለና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መልኩ መከናወኑን ይታዘባል፣ ውሳኔዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣ በስራ ምክንያት የተከሰቱ ችግሮች እንዲታረሙ ለአመራሩ አስተያየት ይሰጣል

22.2.9. የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣

22.2.10. የቁጥጥር ኮሚቴ የስራ አፈጻጸም ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፣

22.2.11. የኅ/ሥራ ማኅበሩ ቅጥር ሰራተኞች ኃለፊነታቸውን በአግባቡ ስለመወጣታቸው ክትትል ያደርጋል፣ የተከሰቱ ግድፈቶች እንዲታረሙ ለስራ አመራር ኮሚቴ ሪፖርት ያደርጋል፣

22.2.12. ሌሎች በጠቅላላ ጉባኤ የሚወሰኑ ውሳኔዎችን ተግበራዊ ያደርጋል፣

23. የንዑሳን ኮሚቴዎች አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር፤

23.1. የንዑሳን ኮሚቴዎች አደረጃጀት

የስራ አመራር ኮሚቴው በተሰጠው ስልጣን መሰረት ለስራው አስፈላጊ የሆኑ የተለያዩ ንዑሳን ኮሚቴዎችን በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ያደራጃል፣ ተግባራና ሀላፊት ይሰጣል፣ ይገመግማል፣

23.1.1. ንዑሳን ኮሚቴዎች የሚደራጁት በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ይሆናል፤

23.1.2 ኮሚቴዎቹ እያንዳንዳቸው አምስት አባላት ይኖራቸዋል፣ የየራሳቸው ሰብሳቢ፣ ፀሀፊና አባል ይኖራቸዋል፣

23.1.3 ኮሚቴዎቹ ተጠሪነታቸው በዋና ጽ/ቤቱ ለተቋቋመው የስራ አመራር ኮሚቴ ነው፣ የስራ አፈጻጸም ሪፖርታቸውን እንዲሁም እቅድና በጀት ለስራ አመራር ኮሚቴ ያቀርባሉ፣ ያጸድቃሉ፣ ተግባራዊ ያደርጋሉ፣

23.1.4 ዝርዝር ተግባር አፈጻጸማቸው ከኅብረት ሥራ ማህበሩ በሚያዘጋጀው ውስጠ ደንብ የሚገለጽ ይሆናል፣

23.1.5 የኮሚቴዎቹ የስራ ዘመን የስራ አመራሩ ኮሚቴ የስራ ዘመን ይሆናል፣

23.2. የቁጠባና ብድር ኮሚቴ ስልጣንና ተግባራት፡

23.2.1. ከኅብረት ሥራ ማኅበሩ አባላት የሚቀርቡ የብድር ጥያቄዎች በመተዳደሪያ ደንብና በውስጥ የብድር አስተዳደር ደንብ መሠረት መሆኑን አረጋግጦ ብድሩ እንዲፈቀድ የውሳኔ ሃሳብ ለቅርንጫፍ ሰብሳቢ ያቀርባል፤ የብድር መጠኑ ከቅ/ጽ/ቤት በላይ ከሆነ ለዋና ጽ/ቤት ሥራ አመራር ኮሚቴ ያቀርባል፤

23.2.2. አባላት ለብድር ማስያዣ ያቀረቧቸው ዋስትናዎች ትክክለኛነታቸውን ያረጋግጣል፣በአግባቡ መያዛቸውን ይከታተላል፤

23.2.3. የብድር ጠያቂዎችን የዋስትና አቅም በመገምገም የጠየቁት ብድር በተፈለገው ግዜ ውስጥ መመለስ መቻላቸውን ይመረምራል፤

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
መዝገብ ቤት
Archive
Ethiopian Cooperative Commission Archive

23.2.4. የኅብረት ሥራ ማኅበሩን የብድር አጠቃቀምና አመላለስ ይከታተላል፤

23.2.5. ስለብድር ጥያቄ አቀራረብ፤ አሰጣጥ፣አመላለስና በሌሎች ብድር ነክ ጉዳዮች ላይ ዕቅድ በማዘጋጀት ለሥራ አመራር ኮሚቴ ያቀርባል፣ሲፈቀድ ይተገብራል፤

23.2.6. የብድር መክፈያ ግዜን ማራዘምና ተጨማሪ ብድር የተጠየቀባቸውን ብድሮች መርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለቅርንጫፍ ስብሳቢ ወይም ለሥራ አመራር ኮሚቴ ያቀርባል፣

23.2.7. አዳዲስ የብድር አሰራር ሃሳብ ያፈልቃል፣ ለቅርንጫፍ ሰብሳቢ ወይም ለሥራ አመራር ኮሚቴ ያቀርባል፤

23.2.8. ወቅታዊ የሥራ ሪፖርት ለሥራ አመራር ኮሚቴ ያቀርባል፤

23.2.9. ለአባላት በብድር የተሰጠውን ገንዘብ እስከነወለዱ በወቅቱ እንዲመለስ ክትትል ያደርጋል፣ በወቅቱ ያልተመለሱ ብድሮች ያልተመለሱበትን ምክንያት ያጣራል ውጤቱንም ለሥራ አመራር ኮሚቴ ያሳውቃል፤

23.2.10. በየግዜው የሚሰሩ ሥራዎችን መዝግቦ ያስቀምጣል፤

23.2.11. ሌሎች በሥራ አመራር ኮሚቴ የሚሰጡትን ሥራዎችን ይተገብራል፤

23.2.12. የኅብረት ሥራ ማኅበሩ የብድር ኮሚቴው ሌሎች ዝርዝር ተግባራት በብድር መመሪያው መሠረት ያከናውናል፡፡

23.3. የትምህርትና ቅስቀሳ ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር

የኅብረት ሥራ ማኅበሩ ወለድ አልባና ወለድ የሚያስገኙ አገለግልቶችን የሚሰጥ ከሆነ የትምህርትና ቅስቀሳ ኮሚቴ ለሁለቱም አገልግሎቶች ራሳቸውን አስችሎ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

23.3.1. ለአባላት፣ ለኮሚቴ አባላት፣ ለቅጥር ሠራተኞችና ለአካባቢው ማህበረሰብ ትምህርትና ስልጠና ያመቻቻል፤

23.3.2. ህብረተሰቡንና አባላትን ስለ ገንዘብ አጠቃቀምና ቁጠባ ምክር በመስጠት የበለጠ እንዲቆጥቡና በአኗኗራቸው በተጨባጭ ለውጥ እንዲያስመዘግቡ ያስተምራል፣ ይቀሰቅሳል፤

23.3.3. አባላት የሚወስዱት ብድር ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲያውሉት እና የወሰዱትን ብድር በብድር ውሉ መሠረት እንዲመልሱ ለማስቻል ትምህርት ይሰጣል፤

23.3.4. የተለያዩ ፅሁፎችንና ዶክሜንቶችን መገዛታቸውንና መዘጋጀታቸውን ያረጋግጣል፤

23.3.5. የኅብረት ሥራ ማኅበራት ቀን እንዲከበር ያስተባብራል፤

23.3.6. የኅብረት ሥራ ማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብና ውስጠ ደንብ አባላት እንዲያውቁት ያደርጋል፤

23.3.7. ከሥራ አመራር ኮሚቴ ጋር በመሆን የጉብኝትና የልምድ ልውውጦችን ያመቻቻል፤

23.3.8. ለአባላት መደረግ ስለሚገባው ትምህርትና ስልጠና በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ዕቅድ ያወጣል፣ በሥራ አመራር ኮሚቴ ሲፈቀድ ተግባራዊ ይደረጋል፤

23.3.9. ለትምህርት ወይም ለስልጠና የተመደበ ገንዘብ መኖሩን ማረጋገጥ፣ ተግባራዊ ማድረግ፤

23.3.10. በኅብረት ሥራ ማኅበሩ እየተሰሩ ያሉ ስራዎችን እየዘገበ ለአባላት ያሳውቃል፤

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
መዝገብ ቤት
Archive
Ethiopian Cooperative Commission Archive

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Keleta Youth Primary SACCO Ltd.

23.3.11. የተለያዩ ጠቃሚ የሆኑ ፅሁፎችን በማሰባሰብ አባላት ሊያገኙ የሚችሉበትን መንገድ ያመቻቻል፤

23.3.12. ለሥራ አመራር ኮሚቴ የሥራ ሪፖርትና ዕቅድ አዘጋጅቶ ያቀርባል፤

23.3.13. ሌሎች ከሥራ አመራር ኮሚቴ የሚሰጡትን ሥራዎች ያከናውናል፣

23.4. የወለድ አልባ ብድር ኮሚቴዎች

በአንቀጽ 31.2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪም የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል።

23.4.1. የወለድ አልባ ብድር ጥያቄ ከተጠቃሚ አባላት መቀበል፤

23.4.2. የወለድ አልባ ብድር ጥያቄን እንደ አገልግሎቱ ዓይነት መሰረት በማድረግ መገምገምና ለውሳኔ ማቅረብ፤

23.4.3. ለወለድ አልባ ብድር የሚውል በቂ ገንዘብ ስለመኖሩ ማረጋገጥ፤

23.4.4. የወለድ አልባ ብድር አመላለስን መከታተል፤

23.4.5. በወለድ አልባ የተሰጠው ብድር ከሸሪዓ ህግ ጋር በማይቃረኑ የስራ መስኮች ላይ መዋሉንመከታተል፤

24. የኅብረት ሥራ ማህበሩቅጥር ሰራተኞች

24.1. ኅብረት ሥራ ማህበሩየሰው ሀይል አስተዳደር መመሪያና በጠቅላላ ጉባኤ የጸደቀየአደረጃጀት መዋቅር ይኖረዋል፣

24.2. የኅብረት ሥራ ማህበሩ የእለት ከእለት ስራዎችን የሚያከናውኑ ቅጥር ሰራተኞች ይኖሩታል፣

24.3. ቅጥር ሰራተኞች በሰው ሀይል አስተዳደር መመሪያና አግባብ ባለው አካል በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የሚተዳደሩ ይሆናል፣

24.4. የቅጥር ሰራተኞችን የሚመራ እና የኅብረት ሥራ ማኅበሩን በኃላፊነት የሚያስተዳድር ዋና ስራ አስፈጻሚ ይኖረዋል፣

24.5. የኅብረት ሥራ ማኅበሩዋና ስራ አስፈጻሚ፣ ም/አስፈፃሚዎች፣ የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ስራ አስኪያጆች እና ሌሎች ቅጥር ሰራተኞችን ሲቀጠር አግባብ ባለው ባለስልጣን በሚያወጣው መመሪያ መመሰረት ተፈጻሚ መሆን አለበት፣

25. የኅብረት ስራ ማህበሩ ቅጥር ሰራተኞች ተግባርና ሃላፊነት

25.1. የኅብረት ሥራ ማህበሩዋና ስራ አስፈጻሚ ተግባርና ኃላፊነት

25.1.1 የኅብረት ሥራ ማህበሩን የዕለት ተዕለት የሥራ እንቅስቃሴ በኃላፊነት ይመራል፣

25.1.2 የኅብረት ሥራ ማህበሩን ስትራቴጅክና ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ እና በጀት በማዘጋጀት ለሥራ አመራር ኮሚቴ ያቀርባል ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችም ያከፋፍላል፣

25.1.3 የኅብረት ሥራ ማህበሩተቀጣሪ ሰራተኞች በሰው ሀይል አደረጃጀትና አስተዳደር መመሪያ እና አግባብ ባለው ባለስልጣን በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይቀጠራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሳድጋል፣ ያሰናብታል፣

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
መዝገብ ቤት
Archive
Ethiopian Cooperative Commission Archive
The Federal Democratic Republic Ethiopia Kefeta Youth Primary SACCO Ltd.Liab

25.1.4 የአባላትን ፍላጎት መሰረት በማድረግ የተለያዩ ቁጠባ፣ ብድርና የአነስተኛ ኢንሹራንስ አገልግሎቶች እንዲቀረጹና እንዲስፋፉ ያደርጋል፣

25.1.5 የኀብረት ስራ ማህበሩን የስራ አፈጸፀም ከሰራተኞች ጋር በመሆን ይገመግማል፤ ሪፖርቱን ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣

25.1.6 በኀብረት ሥራ ማህበሩየብድር ውሎችን፣ የቁጠባ ወጭዎችንና አስተዳደራዊ ወጭዎችንክፍያ ይፈፅማል፣

25.1.7 በኀብረት ሥራ ማህበሩየሥራ አመራር ኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ ያለ ድምጽ ይገኛል፤ ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል፤ አስተያየት እና መረጃ ይሰጣል፣

25.1.8 የኀብረት ሥራ ማህበሩን ጽህፈት ቤት ያደረጃል፣ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ እንዲፈጠር ያደርጋል፣

25.1.9 ቢሮዎች ለስራ ምቹ እንዲሆኑ ያደርጋል፣ የአባላትን መረጃዎችና ፋይሎች በተገቢው ሁኔታ እንዲደራጁ ያደርጋል፣

25.1.10 ሸሪዓ መር የቁጠባና ብድር አገልግሎቶችን እንዲሁም የአነስተኛ መድን ዋስትና ወይም የተካፉል አገልግሎቶችን ይተገብራል።

25.1.11 ኀብረት ስራ ማህበሩ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶችን ያስተዋውቃል፣

25.1.12 የኀብረት ስራ ማህበሩን መተዳደሪ ደንብ ማሻሻያ፣ ውስጠ ደንብ፣ የብድር ፣ የቁጠባ፣ የሰው ሀብት አስተዳደር፣ የንብረት አስተዳደር ፣ የሂሳብ አያያዝና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ የአሰራር ስርዐቶችን እንዲዘጋጁ ያደርጋል ሲፈቀደም ይተገብራል፣

25.1.13 የኀብረት ስራ ማህበሩ የሚያደርጋቸውን ኢንቨስትመንቶችን በመለየት የአዋጭ ጥናት ያስጠናል፣ ፕሮጀክቶችን ያዘጋጃል ሲፈቀደም ተግባራዊ ያደርጋል፣

25.1.14 የስራ አመራር ኮሚቴው በሰጠው ስልጣን መሰረት ከአቻ ኀብረት ስራ ማህበራትና ከሌሎች ተቋማት ጋር የስራ ግንኙነት ያደርጋል፣

25.1.15 የኀብረት ስራ ማህበሩን ሂሳብና ስራ አፈጻፀም ኦዲት ያስደርጋል፣

25.1.16 ከሥራ አመራር ኮሚቴ እና ቁጥጥር ኮሚቴ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፤

25.2 የኀብረት ሥራ ማህበሩ ምክትል ስራ አስፈጻሚ ተግባርና ኃላፊነት

25.2.1. የኀብረት ስራ ማህበሩን ለዋና ስራ አስፈፃሚ ተጠሪ የሆኑ ምክትል ስራ አስፈጻሚዎች ይኖሩታል፣

25.2.2 የተመመደቡቡትን የስራ ክፍል ተግባራትን ያቅዳል፣ ያቀናጃል፣ ይተግብራል አፈፃፀሙን ሪፖረት ያደርጋል፣

25.2.2 በስሩ ያሉ ሰራተኞችን ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይገመግማል፣

25.2.3. በስሩ ያሉ ቅርጫፍ ፅ/ቤት ስራ አስኪያጆችን ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይገመግማል፣

25.3. የቅርንጫፍስራአስኪያጅተግባርናሀላፊነት

25.3.1.በቅርንጫፍ ጽ/ቤት ስር ያሉ ሰራተኞችን ያስተዳድራል፣ ይመራል፣ ይገመግማል

25.3.2.የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ስራዎችን መነሻ እቅድ በማቀድ ለዋና ጽ/ቤት ያቀርባል፣

የኢትዮጵያ ኀብረት ሥራ ኮሚሽን
መዝገብ ቤት
Archive
Ethiopian Cooperative Commission · Archive

Federal Democratic Republic Ethiopia Kefeta Youth Primary SACCO Ltd.

25.3.3. ከዋና ጽ/ቤት የተሰጡ እቅዶችንና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በተጨማሪነት የሚታቀዱ እቅዶችን እንዲተገበሩ ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ የአፈፃፀም ሪፖርት ለዋና ጽ/ቤት ያቀርባል፣

25.3.4. በአካባቢው ያሉ ወጣቶች የፋይናንስ አገልገሎት አጠቃቀም ትምህርትና ስልጠና እንዲሰጥ ያደርጋል፤ አዳዲስ አባላት ያፈራል፣

25.3.5. የኅብረት ስራ ማህበሩን የሚሰጣቸውን የፋይናንስ አገልግሎቶች በማስተዋወቅ ቁጠባን በስፋት ያሰባስባል፣

25.3.6. እስከ ተፈቀደለት የብድር ጣሪያ መሰረት በማድረግ ብድር ይሰጣል፣ ከጣሪያ በላይ የሆኑትን የብድር ጥያቄዎችን በማጣራትና አስፈላጊ መረጃዎችን በማደራጀት ለዋና ጽ/ቤት እንዲፀድቅ ይልካል፣ የብድር አመላለስን ይከታተላል፣ ያስመልሳል፣ አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎት ተግባራዊ ያደርጋል፣

25.3.7. የአነስተኛ ኢንሹራንስ ተጠቃሚ አባላት ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን በማጣራት ለዋና ጽ/ቤት መላክና ክፍያ እንዲፈፀም ክትትል ያደርጋል፣

25.3.8. በአካባቢው ካሉ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር የስራ ግንኙነት ያደርጋል፣

25.3.9. የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱን የአገልግሎት አሰጣጥ እርካታ ያለበትን ደረጃ ለመገምገም የሚያስችል አሰራር ይዘረጋል፤ የሚነሱ ቅሬታዎች እንዲፈቱ ያደርጋል፣

25.3.10. የቅርንጫፍ ጽ/ቤት የተሰጠውን ፋይናንስና ንብረት ያስተዳድራል፣

25.4 የሌሎች ቅጥር ሰራተኞች ተግባርና ሀላፊነት

በስራ ዝርዝራቸው የተሰጡ ተግባሮችን ያከናውናሉ፣የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ለቅርብ ሃላፊው ያቀርባሉ፣

26. የኅብረት ሥራ ማህበሩየስብሰባ ሥነሥርዓት፣

26.1. የኅብረት ሥራ ማህበሩመደበኛ ወይም አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ይኖሩታል፣

26.2. የኅብረት ሥራ ማህበሩጠቅላላ ጉባኤ ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ ይደረጋል፣

26.3. የኅብረት ሥራ ማህበሩመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ካሉት አባላት ውስጥ ከግማሽ በላይ ሲገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፣

26.4. መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ተጠርቶ ምልዓተ ጉባኤ ካልተሟላበ15(አስራ አምስት) ቀናት ውስጥ ሁለተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ ይደረጋል፣

26.5. ለሁለተኛ ጊዜ የተጠራው መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ምልዓተ ጉባኤው ካልተሟላ በእለቱ በተገኙ አባላት መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ሊካሄድ ይችላል፣

26.6. በአንቀጽ 26.5 መሰረተ ምልዓት ጉባኤው ሳይሟላ የተካሄደ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ የሚያሳልፋቸው ውሳኔዎች ሁሉም የጉባኤው አባላት በተገኙበት እንደተላለፈ ይቆጠራል፣

26.7. የኅብረት ሥራ ማህበሩስራ አመራር ወይም የቁጥጥር ኮሚቴ ወይም ከጠቅላላ አባላት ውስጥ ከአንድ ሶስተኛ ያላነሱ አባላት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራላቸው ሲጠይቁየኅብረት ሥራ

ኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
መዝገብ ቤት
Archive
Ethiopian Cooperative Commission Archive
The Federal Democratic Republic Ethiopia Kefeta Youth Primary SACCO Ltd.

ማህበሩስራ አመራር ኮሚቴ በ15 (አስራ አምስት አምስት) ቀናት ውስጥ ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ ያደርጋል፣

26.8. የተጠራው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ምልዓተ ጉባኤ ካልተሟላ የስራ አመራር ኮሚቴ አግባብ ላለው ባለስልጣን በሪፖርት ያሳውቃል፣

26.9. የስራ አመራር ኮሚቴ በቀረበለት ጥያቄ መሰረት አስቸኳይ የጠቅላላ ጉባኤውን ካልጠራ የኅብረት ሥራ ማህበሩአባላት ወይም የቁጥጥር ኮሚቴ አግባብ ላለው ባለስልጣን አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲጠራ መጠየቅ ይችላሉ፣

26.10. ከጠቅላላ አባላት ውስጥ ሁለት ሶስተኛ አባላት የተገኙበት አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፣

26.11. የስራ አመራር እና የቁጥጥር ኮሚቴ የራሳቸው መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባ ይኖራቸዋል፣ ዝርዝር አሰራሩ በስራ አመራር ወይም ቁጥጥር ኮሚቴ ውስጠ ደንብ የሚገለጽ ነው፣

27. የኮሚቴ አባላት እገዳና ስንብት

27.1. የኅብረት ሥራ ማህበሩየስራ አመራር ኮሚቴ እና ሌሎች ንዑሳን ኮሚቴ አባል ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ሲያጋጥመው ከአመራርነት ለመሰናበት ከፈለገ ለስራ አመራር ኮሚቴ ማመልከቻ ማቅረብ ይኖርበታል፣

27.2. የኅብረት ሥራ ማህበሩ ቁጥጥር ኮሚቴ አባል ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ሲያጋጥመው ከአመራርነት ለመሰናበት ከፈለገ ለቁጥጥር ኮሚቴ ማመልከቻ ማቅረብ ይኖርበታል፣

27.3. የስራ አመራር ወይም የቁጥጥር ኮሚቴ የስንብት ጥያቄ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ በ15(አስራ አምስት)ቀናትውስጥ በጽሁፍ መልስ መስጠት ይኖርበታል፣

27.4. የስራ አመራር ወይም የቁጥጥር ኮሚቴ ተመራጭ ከኅብረት ሥራ ማህበሩደንብና ህግን የሚጻረር ድርጊት ከፈጸመ ተጠሪ በሆነበት የስራ አመራር ወይም ቁጥጥር ኮሚቴ አማካኝት ከስራው ይታገዳል፣

27.5. የታገደው አመራር የታገደበት ምክንያት በጽሁፍ እንዲያውቀው በማድረግ ለጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ ውሳኔ እንዲሰጠው ይደረጋል፣

27.6. አንድ አመራር ለ3(ሰስት) ተከታታይ የኅብረት ሥራ ማህበሩስራዎችና ስብሰባዎች እንዲገኝ ጥሪ ተደርጎለት ያለበቂ ምክንያት ካልተገኘ ከአመራርነቱ ታግዶ ለጠቅላላ ጉባኤ እንዲወሰንበት ይቀርባል፣

28. ድርሻና ጥቅምን ስለማስከበር፣ ስለማቻቻልና ስለማስተላለፍ፣

28.1. አንድ አባል ከአባልነት የሚሰናበት ከሆነ በኅብረት ሥራ ማህበሩየሚኖረውን ድርሻና ጥቅም የሚከፈለው በኅብረት ሥራ ማህበሩያለበት እዳ ከተቀነሰ በኋላ የሚቀረው ብቻ ነው፣

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
መዝገብ ቤት
Archive
Ethiopian Cooperative Commission
Federal Democratic Republic Ethiopia Kefeta Youth Primary SACCO Ltd

28.2. አንድ አባል የኅብረት ሥራ ማህበሩውስጥ ያለው ጥቅሙ ወይም ድርሻ ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ውጭ ላለበት እዳ ወይም ተጠያቂነት ሊከበር፣ ሊያዝ ወይም ሊሸጥ አይችልም፣

28.3. የኅብረት ሥራ ማህበሩከአባሉ ላይ ለሚፈልገው እዳ የአባሉን ድርሻ እና ሌሎች ጥቅሞች ወይም ካለው የቁጠባ ገንዘብ ላይ በመቀነስ እዳውን ያቻችላል፣

28.4. ወራሹ የኅብረት ሥራ ማህበሩአባል ለመሆን ከፈለገ የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟላ ከሆነ አባል ሊሆን ይችላል

29. **የቁጠባ አሰራር፣**

29.1 **ወለድ የሚያስገኝ ቁጠባ አገልግሎት አሰጣጥ**

29.1.1. ኅብረት ሥራ ማህበሩ ወለድየሚያስገኝ መደበኛ ቁጠባ ከአባላት መሰብሰብ አለበት፣

29.1.2. ኅብረት ስራ ማህበሩ የአንድ አባል ዝቅተኛው ወርሀዊ መደበኛ ቁጠባ ይወስናል፤ ዝቅተኛው ወርሀዊ መደበኛ ቁጠባ እና ዝርዝር የመደበኛ ቁጠባ አፈጻጸም በኅብረት ሥራ ማህበሩ የቁጠባ አስተዳደር መመሪያ የሚቀመጥ ይሆናል፣

29.1.2. እያንዳንዱ አባል ለመቆጠብ ቃል የገባውን መበደኛ ቁጠባ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ገቢ ማድረግ አለበት፣

29.1.3. አንድ አባል የመደበኛ ቁጠባውን መጠን መጨመር ወይም መቀነስ ይችላል፡፡ ሆኖም የቁጠባ መጠኑ ከተቀመጠው አነስተኛ የመደበኛ ቁጠባ መጠን በታች መሆን አይችልም፣

29.1.4. የመደበኛ ቁጠባ ተቀማጭ ገንዘብ የብድር መጠንን ለመወሰን እና ለአባሉ ወይም ለሌላ አባል የብድር ዋስትና ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፣

29.1.5. አባሉ ከኅብረት ሥራ ማህበሩ እስካለቀቀ ድረስ መደበኛ ቁጠባውን ማውጣት አይችልም፣ሆኖም የኅብረት ስራ ማህበሩ የውስጥ የቁጠባ መመሪያ ላይ ደንግጎ ከተወሰነ የቁጠባ መጠን በላይ ያለውን አባሉ ወጪ እንዲያደርግ ሊፈቅድ ይችላል፣

29.1.6. ኅብረት ሥራ ማህበሩ የተለያዩ የፍላጎት ቁጠባዎችንመሰብሰብ ይችላል፣

29.1.7. ቆጣቢዎች የፍላጎት ቁጠባ ገንዘብ በማንኛውም ጊዜ ማውጣት ይችላሉ፣ ሆኖም ገንዘቡ ወጪ መሆን የሚችለው በብድር ዋስትናነት ካልተያዘ ብቻ ይሆናል፣

29.1.8. አንድ ቆጣቢ በኅብረት ሥራ ማኅበሩ ውስጥ በፍላጎት ከቆጠበው የቁጠባ መጠን ውስጥ በአንድ ጊዜ እስከ ተወሰነ የብር መጠን ድረስ ማውጣት የሚችል ሲሆን ከተቀመጠው በላይ ወጪ ለማድረግ የሚጠየቁ ወጪዎች ቆጣቢው ከ 15 ቀን በፊት መጠየቅ የሚኖርበት ስሆን ዝርዝር አፈጻጸም በኅብረት ሥራ ማህበሩ የቁጠባ አስተዳደር መመሪያ የሚቀመጥ ይሆናል፣

29.1.9. የተሰበሰበ የቁጠባ ገንዘብ የኅብረት ሥራ ማህበሩ በስሙ በከፈተው ወለድ በሚያስገኝ የባንክ አካውንት መቀመጥ ይኖርበታል፣

29.1.10. በብሄራዊ ባንክ የተቀመጠው የወለድ ምጣኔ መነሻ ሆኖ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ለሚሰጠው የቁጠባ አገልግሎት የተለያየ አይነት የወለድ ተመን በጠቅላላ ጉባኤ እያጸደቀ ተግባራዊ ያደርጋል፣

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን መዝገብ ቤት Archive Ethiopian Cooperative Commission
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Kefeta Youth Primary SACCO Ltd.

29.1.11. ወለድ የሚታሰብባቸው የቁጠባ ሂሳቦች ወለድ መታሰብ የሚጀምረው ቁጠባው በማህበሩ ሂሳብ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፣ ወለዱ በየወሩ ሂሳቡ ተሰርቶ ወደ አባላት ቁጠባ ሂሳብ ተዛውሮ መቀመጥ ይኖርበታል፣

29.1.12. ኅብረት ስራ ማኅበሩ የሚከፍለው የቁጠባ ወለድ መጠን እና ዝርዝር የአከፋፈል ሁኔታ በቁጠባ መመሪያ ላይ በማካተት ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

29.1.13. ኅብረት ሥራ ማህበሩ የቁጠባ አገልግሎቶችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ የተለያዩ የሂሳብ ሰነዶች፣ መዛግብቶች፣ ካዝናዎች፣ የክፍያ መስኮቶች ማዘጋጀት አለበት፣

29.1.14. የኅብረት ሥራ ማህበሩ የቁጠባ መጠን ለማሳደግና እና ለማበረታታት ሲባል ለአባላት የተለያዩ ማበረታቻዎችን አዘጋጅቶ መስጠት ይቻላል፣

29.1.15. ኅብረት ሥራ ማህበሩ በስራ ክልሉ ውስጥ የፋይናንስ ተጠቃሚ ያልሆኑ የወጣት ክፍሎችን ማካተት እንዲቻል ተስማሚ የሆኑ የቁጠባ አይነቶችን በመቅረጽ ወይም ከሌሎች የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማህበራት በመውሰድ ተጠቃሚ እንዲሆን ማደረግ ይኖርበታል፣

29.2. የወለድ አልባ የቁጠባ አገልግሎት አሰጣጥ

29.2.1. ኅብረት ሥራ ማህበሩ የሸሪዓ ህግን መሰረት ያደረገ መደበኛ ወዲዓ የድ ደማን ወለድአልባመደበኛ ቁጠባ ከአባላት መሰብሰብ ይችላል፣

29.2.2. ኅብረት ሥራ ማህበሩለወለድ አልባየቁጠባ አገልግሎቶችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ የተለያዩ የሂሳብ ሰነዶች፣ መዛግብቶች፣ ካዝናዎች፣ የክፍያ መስኮቶች ያዘጋጃል፣

29.2.3. የወለድ አልባ ቁጠባ አገልግሎት ሲሰጥ ስራውን ለማከናወን የሸሪያ ህግን በሚያውቁ ባለሙያዎችና ራሱን በቻለ የሂሳብ አሰራር መሆን ይኖርበታል፣

29.2.4. ኅብረት ሥራ ማህበሩ ወለድ አልባ የሆነ የፍላጎት ቁጠባ መሰብሰብ ይችላል፤ እነዚህ የወለድ አልባ የቁጠባ አገልግሎቶች ቀርድ ሀሰን፣ ወዲዓ የድ ደማን የመሳሰሉትን የወለድ አልባ አገልግሎቶች ይሰጣል፣

29.2.5. በወለድ አልባ ለተቀመጠ ቁጠባ ወለድ አይጠየቅበትም ወይም አያስገኝም ሆኖም የኅብረት ስራ ማህበሩ ለአባሉ የተለያዩ ማበረታቻዎችን ሊሰጥ ይችላል፣

29.2.6. ኅብረት ስራ ማህበሩ ወለድ አልባ- ቁጠባ የሚቀመጥበት የተለየ ሂሳብ ከፍቶ ማስመጥ ይኖርበታል፣

30. ስለ ብድር አስተዳደር፣

30.1. የኅብረት ሥራ ማህበሩ በጠቅላላ ጉባኤ የጸደቀ የብድር አስተዳደር መመሪያ ይኖረዋል፣

30.2. የኅብረት ሥራ ማህበሩብድር ስርጭት ተፈፃሚ የሚሆነው በኅብረት ሥራ ማህበሩመተዳደሪያ ደንብና የብድር አስተዳደር መመሪያ መሰረት መሆን አለበት፣

30.3. የኅብረት ሥራ ማህበሩ ለአባላት የአጭር ጊዜ፤የመካከለኛ ጊዜ እና የረጅም ጊዜ ብድር ሊሰጥ ይችላል፡

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
መዝገብ ቤት
Archive
Ethiopian Cooperative Commission Archive

Federal Democratic Republic Ethiopia Keleta Youth Primary SACCO Ltd Liab

30.4. ማንኛውም በዋና ቢሮ የሚሰጥ ብድር የሚሰጠው በብድር ክፍል ሃላፊወይም በብድር ባለሙያ ተገምግሞ ሲፀድቅ መሆን አለበት፣በቅርንጫፍ ደረጃ የሚሰጥ ብድር በዉስጠ ደንብ ይገለፃል፡፡

30.5. ኅብረት ሥራ ማህበሩብድር የሚሰጠው ለአባሉና ለኅብረት ሥራ ማህበራት ብቻ ይሆናል፣

30.6. የኅብረት ስራ ማህበሩ የሚሰጠው ብድር በግል ወይም በቡድን ሊሆን ይችላል፤ በቡድን ለሚሰጥ ብድር ዝርዝር አፈፃፀም በብድር አስተዳደር መመሪያ ላይ ይገለፃል፣

30.7. የኅብረት ስራ ማህበሩ በቡድን ለሚሰጠው የቡድን ብድር የአባላት ብዛት ከ2 እስከ 7 ሆኖ ሁሉም የኅብረት ስራ ማህበሩ አባላት መሆን አለባቸው፣

30.8. አንድ አባል የሚፈለግበትን የአባልነት ግዴታ ከተሟላበት ከ 3ወር ጀምሮ የብድር አገልግሎት የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡ ሆኖም የብድሩ አሰጣጥ መነሻ የሚያደርገው አባሉ በኅብረት ሥራ ማህበሩ ባለው ቁጠባና የአባላት እጣ ላይ ተመስርቶ መሆን አለበት፣

30.9. የኅብረት ሥራ ማህበሩለብድር አገልግሎት የሚያውለው ገንዘብ መጠን ከኅብረት ሥራ ማህበሩጠቅላላ ሀብት ከ80(ሰማንያ) በመቶ መብለጥ የለበትም፣

30.10. ኅብረት ስራ ማህበሩ ለአንድ አባል የሚያበድረው የብድር ጣሪያ መጠን ዝርዝር አፈጻጸም በኅብረት ሥራ ማህበሩ የብድር አስተዳደር መመሪያ የሚቀመጥ ይሆናል፣

30.11. ከግለሰብ አባል በተጨማሪ ኅብረት ስራ ማህበሩ በቡድን የሚሰጠው የብድር ጣሪያ መጠንዝርዝር አፈፃፀምበኅብረት ሥራ ማህበሩ የብድር አስተዳደር መመሪያ የሚቀመጥ ይሆናል፣

30.12. የኅብረት ሥራ ማህበሩለሚሰጣቸው የብድር አገልግሎቶች ተመጣጣኝ የሆነ ዋስትና ከተበዳሪዎች መጠየቅ አለበት፣

30.13. የኅብረት ሥራ ማህበሩለብድር አስተዳደር አመች የሚሆኑ ወለድ የሚታሰብባቸውና የማይታሰብባቸው የብድር መመዝገቢያ ሰነዶች፣ መዝገቦችና ቅጾች ማዘጋጀት አለበት፣

30.14. የኅብረት ሥራ ማህበሩየአባላቱን ፍላጎት መሰረት በማድረግ የተለያዩ የብድር አይነቶችይቀርጻል፣ ያስተዋውቃል፣

30.15. የኅብረት ሥራ ማህበሩብድር ከመሰጠቱ በፊት የኅብረት ሥራ ማህበሩሂሳብ ያለበት ሁኔታ የሚገልጽ ዝርዝር ሪፖርት ማዘጋጀት ይኖርበታል፣

30.16. የኅብረት ሥራ ማህበሩየሚያሰራጫቸውን ብድሮች የመመለሻ ጊዜያቸውን በመለይት ክትትል ያደርጋል፣

30.17. ከአቅም በላይ የሆነና የማይመለስ ብድር በመጠንና በአይነት ተለይቶ በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ እንዲሰጥበት ይደረጋል፣

30.18. የሥራ አመራር ኮሚቴ በበጀት ዓመቱ ከፋይናንስ ተቋማት ለሚበደረው ብድር የጠቅላላ ጉባኤ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፣

31. የሸሪዓ መር ወለድ አልባ የብድር አገልግሎቶች

31.1. የኅብረት ሥራ ማህበሩወለድ አልባ የሆነ የብድር አገልግሎት ለአባሉ ሊሰጥ ይችላል፣ ለሚሰጠው ብድር ምንም አይነት ወለድ ማስከፈል ወይም መቀበል አይችልም፡፡

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን መዝገብ ቤት Archive
Federal Democratic Republic of Ethiopia Kefeta Youth Primary SACCO Ltd.

31.2. የኅብረት ሥራ ማህበሩየሚሰጠው የወለድ አልባ ብድር አገልግሎቶች የኅብረት ሥራ ማህበሩን አቅም እና የአባላት ፍላጎት መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፣

31.3. የኅብረት ሥራ ማህበሩለአባላት የሰጠውን ሸሪዓ መር የብድር አገልግሎት ለማስተዳደር የሚያስፈልጉ አሰራሮች፣ ሰነዶች፣ መዛግብቶች እና ቅፆች ማዘጋጀት አለበት፣

31.4. የወለድ አልባ የብድር አገልግሎት መሰረት የሚያደርገው ግዥና ሽያጭን አሰራር መሰረት በማድረግየአባላትን ጥያቄ መሰረት በማድረግ ሆኖ ዝርዝር አሰራሩ በብድር አስተዳደር መመሪያ ይገለጻል፣

31.5. ከወለድ አልባ የሚሰበሰብ ብድር ገቢ የሚሆነው በወለድ አልባ ሂሳብ ቁጥር ውስጥ መሆን አለበት፣

32. ወለድ የሚከፈልባቸው የብድር አገልግሎት

32.1. የኅብረት ሥራ ማህበሩወለድ የሚያስከፍልባቸው የብድር አገልግሎት ይሰጣል፣

32.2. የየኅብረት ሥራ ማህበሩ የብድር ወለድ አሰላል እና መጠን እንደየ ብድር አይነቱ የሚለያይ ሆኖ የሚሰበሰበው የወለድ መጠን በስራ አመራር ኮሚቴ ቀርቦ በጠቅላላ ጉባኤ የሚወሰን ሲሆን ዝርዝር አፈፃፀሙ በኅብረት ስራ ማህበሩ የብድር አስተዳደር መመሪያ መሰረት ተግባራዊ መደረግ አለበት፣

32.3. በወለድ የተሰጠ ብድር ሂሳብ መግባት ያለበት ወለድ በሚያስገኝ ሂሳብ ቁጥር ውስጥ ነው፣

33. የብድር ዋስትና አያያዝ

33.1. ኅብረት ስራ ማህበሩ ያለዋስትና ብድር መስጠት አይችልም፣

33.2. ኅብረት ስራ ማህበሩ ለሚሰጣቸው ብድሮች የሚይዛቸው የዋስትና አይነቶች በሚመለከተው አካል በወጣው መመሪያ መሰረት ሆኖ በራሱ ተጨባጭ ሁኔታ በሚመቸው መያዝ ይችላል፤ ሆኖም ዝርዝር አፈፃፀሙ በብድር አስተዳደር መመሪያ ላይ የሚገለፅ ይሆናል፣

33.3. ኅብረት ስራ ማህበሩ ከሌሎች ተቋማት ለዋስትናነት የሚይዛቸው ንብረቶች ከሚመለከታቸው አካላት ህጋዊነቱን የተረጋገጠና ብድሩ ሳይከፈል ወይም ዋስትናው ሳይቀየር ወደ ሶስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ የታገደ መሆን ይኖርበታል፣

33.4. የኅብረት ስራ ማህበሩ በዋስትናነት የያዘውን ንብረት ሌላ ተመጣጣኝ እስካልቀበ ድረስ ዋስትናውን ማውረድ አይችልም፣

33.5. ኅብረት ስራ ማህበሩ በዋስትናነት የያዘውቸውን ሰነዶች ዋና ኮፒ በኅብረት ስራ ማህበሩ ዋና ፅ/ቤት እንዲሁም ኮፒዉ በቅርንጫፍ ፅ/ቤት ውስጥ በጥንቃቄ መቀመጥ አለበት፣

34. አነስተኛ የመድን ዋስትና ወይም ተካፉል አገልግሎት ስለመስጠት

34.1. የኅብረት ሥራ ማህበሩየአነስተኛ መድን ወይም ተካፉል አገልግሎት በወኪልነት ወይም በራሳቸው ለአባሉ መስጠት ይችላሉ፣

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚ. መዝገብ ቤት Archive Ethiopian Cooperative Commission Archive

34.2. የአነስተኛ መድን ዋስትና አገልግሎት በወለድ ለሚሰጣቸው አባላት የሚሰጥ ሲሆን የተካፋል አገልግሎት ደግሞ ለወለድ አልባ አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን አለባቸው፣

34.3. አነስተኛ መድን ወይም ተካፋል አገልግሎት ከአባላት በሚሰበሰብ አረቦን የሚሸፈን ሲሆን ለዚህ አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማህበሩ የራሱ የሆነ የሂሳብ አሰራር መዘርጋት አለባቸው፣

34.4. ኅብረት ሥራ ማህበሩ አነስተኛ መድን ዋስትና ወይም ተካፋል አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ አዘጋጅቶና በጠቅላላ ጉባኤው አጸድቆ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፣

34.5. ለአረቦን ከተሰበሰበ ገንዘብ ውስጥ የካሳ ክፍያ ተከፍሎ ከቀረው ገንዘብ ውስጥ ለአደጋ መጠባበቂያነት የቁጠባ ሂሳብ ተከፍቶ ተቀማጭ መሆን አለበት፣

34.6. በመጠባበቂያነት የተቀመጠው ገንዘብ አጠቃቀም በተመለከተ አግባብነት ያለው አካል በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ተግባራዊ ይሆናል፤ ቀሪው ገንዘብ በገቢነት ተይዞ ወደ ትርፍ ክፍፍል ይሄዳል፣

34.7. አባላት ከኅብረት ሥራ ማህበሩ የብድርተጠቃሚ ለመሆን ኅብረት ስራ ማህበሩ የአነስተኛ ኢንሹራንስ አገልግሎት መጠቀም ግዴታ አለባቸው፣

34.8. ከተካፋል አገልገሎት ተጠቃሚዎች የሚሰበሰብ ገንዘብ የጉዳት ማካካሻ ተከፍሎ የሚቀረው ገንዘብ ተጠቃሚዎች በሚወስኑት ውሳኔ መሰረት ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል፣

35. የመድን ዋስትና ሽፋን

ኅብረት ሥራ ማህበሩ ንብረቱን ከተለያየ አደጋ ለመጠበቅ እንዲችል የመድን ዋስትና መግባት አለበት፣

36. ስለኅብረት ሥራ ማህበሩ ሂሳብና ገንዘብ አያያዝ፣

36.1. ኅብረት ሥራ ማህበሩ በወለድ አልባ እና ወለድ የሚታሰብባቸው ተብለው የተለዩ ሁለት የተለያዩ የሂሳብ አርዕስቶች ይኖሩታል፤ የገንዘብ አያያዛቸው፣ አመዘጋገባቸው፣ ሪፖርት ዝግጅታቸውና አቀራረባቸው ተለያይተው ይሆናሉ፣ ሆኖም ኅብረት ሥራ ማህበሩ የፋይናንስ አቋም ለማወቅ አንድ ወጥ የሆነ የሂሳብ ሪፖርት ይኖረዋል፣

36.2. የቁጠባ፣ የብድር እና ሌሎች ገቢዎች ሲቀመጡ በወለድ አልባ እና ወለድ የሚታሰብባቸው የሂሳብ ቁጥሮች በባንክተከፍተው መቀመጥ አለባቸው ዝርዝር አሰራሩ በፋይናንስ አስተዳደር መመሪያ ይቀመጣል፣

36.3. ገንዘብ አያያዝ በተመለከተ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ባዘጋጀው የፋይናንስ አስተዳደርመመሪያ መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፣

36.4. የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሂሳብ አያያዝ ዘመናዊ አሰራርን የተከተለ መሆን አለበት፣

36.5. በፋይናንስ አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚከተሉትን የሂሳብ አሰራር ስርዓቶች ይከተላል።

36.5.1. የወለድ አልባ እና ወለድ የሚያስገኝ የቁጠባ ሂሳብ አሰባሰብና አወጣጥ አሰራር ስርዓት

36.5.2. የወለድ አልባ እና ወለድ የሚያስገኝ የብድር አሰጣጥና አመላለስ አሰራር ስርዓት

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን መዝገብ ቤት Archive Ethiopian Cooperative Commission Archive

36.5.3. የአነስተኛ መድን ዋስትና እና ተካፋል አገልግሎት አሰራር ስርዓት

36.5.4. የወጪ አስተዳደርና የትርፍ ክፍፍልአሰራር ስርዓት

36.5.5. የሂሳብ መግለጫና ሪፖርት አቀራረብ አሰራር ስርዓት፣

36.6. የኅብረት ስራ ማህበሩ የሂሰብ አያያዝ የተለያዩ የሂሳብሰነዶች፣መዝገቦችእና ቅጻ ቅጾች ይኖሩታል፣

37. **ስለ ቅጣትና ልዩ ልዩ የአገልግሎት ክፍያዎች፣**

አዋጅን፣ ደንብን ፣ መመሪያንና የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔን ያላከበረ አባል ቅጣት ይቀጣል፣ አፈፃፀሙም በውስጥ ደንብ የሚወሰን ይሆናል፣

38. **የአበልና ሌሎች ክፍያዎች**

ለስራ አመራር እና ሌሎች የኮሚቴ አባላት እንዲሁም ለቅጥር ሰራተኞች የሚከፈል አበል በኅብረት ስራ ማህበሩ ውስጠ ደንብ መሰረትተፈፃሚ ይሆናል፣

39. **የኅብረት ሥራ ማህበሩየገንዘብ ምንጭ፣**

39.1. የመመዝገቢያ ክፍያ፣

39.2. ከአባላት የሚሰበሰብ ዕጣ ክፍያ

39.3. ከትርፍ ላይ ተቀንሶ የሚቀመጥ መጠባበቂያ

39.4. ከተለያዩ አካላት የሚሰጡ ስጦታዎች፣

39.5. ከአባሉ የሚሰበሰብ ቁጠባ

39.6. ከውጭ የሚገኙ የተለያዩ ብድሮች

39.7. ከጥቃቅን ሽያጭ የሚገኝ ገቢ

39.8. ከወለድ የሚገኝ ገቢ

39.9. ከቅጣት የሚገኝ ገቢ፣

39.10. ሌሎች ገቢዎችን ያካትታል፣

40. **የተጣራ ትርፍ ክፍፍል፣**

40.1. የኅብረት ሥራ ማህበሩየተጣራ ትርፍ ውስጥ 30 በመቶ እየተቀነሰ የካፒታሉን 30 በመቶ እስከሚደርስ ድረስ ኅብረት ሥራ ማህበሩበሚከፍተው ቁጠባ ሂሳብ ተቀማጭ ይሆናል፣

40.2. የኅብረት ሥራ ማህበሩመጠባበቂያ ካፒታል የሚፈለገውን መጠን ከደረሰ በኋላ የተጣራ ትርፍ ሙሉ በሙሉ ለትርፍ ክፍፍል ይውላል፣ ሆኖም ህግ በሚያዘው መሰረት ለኅብረት ሥራ ፈንድ የሚሆን ገንዘብ ተቀናሽ መሆን ይኖርበታል፣

40.3. የኅብረት ሥራ ማህበሩመጠባበቂያ ሂሳብ በሚፈለገው ደረጃ መገኘቱን ትርፍ ክፍፍል ከመደረጉ በፊት አግባብ ባለው ባለስልጣን በሚሰይመው ኦዲተር መረጋገጥ ይኖርበታል፣

40.4. ለአባላት የሚከፋፈለው የትርፍ ክፍፍል አደላደልበየአመቱ በጠቅላላ ጉበኤ ቀርቦ የሚወሰን ይሆናል፣

40.5. አባላት ካገኙት አመታዊ ትርፍ ክፍፍል ተጨማሪ እጣ ሊገዙ ይችላሉ፣

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን Ethiopian Cooperative Commission መዝገብ ቤት Archive

Federal Democratic Republic of Ethiopia Kefeta Youth Primary SACCO Ltd.

41. **ስለ ኅብረት ሥራ ማህበሩሂሳብ ወይም በጀት አመት፣**

41.1. የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሂሳብ ወይም በጀት አመት እ.ኤ.አ. ከሀምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 ቀን ድረስ ይሆናል፣

41.2. የኅብረት ሥራ ማህበሩአመታዊ ሂሳብ በ 30 ቀናት ውስጥ ተዘግቶ የፋይናንስ መግለጫዎች መዘጋጀት አለባቸው፣ ለስራ አመራር ቦርድም መቅረብ ይኖርባቸዋል፣

41.3. የበጀት አመቱን ተከትለው ኅብረት ሥራ ማህበሩእቅድና በጀት እንዲሁም የአፈጻጸም ሪፖርት ተዘጋጅተው ለስራ አመራር ኮሚቴና ለጠቅላላ ጉባኤ መቅረብ ይኖርባቸዋል፣

42. የሂሳብ ምርመራ፣

42.1. የኅብረት ሥራ ማህበሩሂሳብ እንዲመረመርለት አግባብ ላለው ባለስልጣን ጥያቄ በማቅረብ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ማስመርመር አለበት፣

42.2. የኅብረት ሥራ ማህበሩሂሳብ ከበጀት አመቱ መጀመሪያ ጀምሮ በ90(ዘጠና) ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ሂሳቡ መመርመር አለበት፣

42.3. የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት ሂሳብ ወለድ ከሚያስገኝ ሂሳብ ለብቻው ተለይቶ ኦዲት መደረግ ይኖርበታል፣

42.4. የሂሳብ ምርመራ ሪፖርት ለኅብረት ሥራ ማህበሩበደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ለጠቅላላ ጉባኤ መቅረብ አለበት፣

42.5. የቀረበው የኦዲት ሪፖርቱ የአሰራር ግድፈቶችና የሂሳብ ጉድለቶች ከታየበት በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ማግኘት ይኖርባቸዋል፣

43. **የፋይናንስ አፈፃፀም መለኪያዎችአተገባበር**

43.1. የኅብረት ሥራ ማህበሩየፋይናንስ አፈጻጸሙን የሚገመግምበት አግባብ ያለው ባለስልጣን በሚያወጣው የፋይናንስ አፈጻጸም መገምገሚያና መከታተያ መመሪያ መሰረት የአሰራር ስርዓት ይኖረዋል፣ የፋይናንስ አፈጻጸም መገምገሚያ መከታተያ ስርዓት በዋናነት በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ማተኮር ይኖርበታል፤-

43.1.1. የሀብት ጥበቃ፣

43.1.2. የሀብት ውጤታማነት፣

43.1.3. የሀብት ጥራት

43.1.4. ትርፋማነት፣

43.1.5. የእዳ መጠን፣

43.1.6. የእድገት ምልክቶች

43.2. የኅብረት ሥራ ማህበሩመዛግብትና ሰነዶች ለተቆጣጣሪ አካል ክፍት መሆን አለባቸው፣ የአመራር አካላትና ቅጥር ሰራተኞች ለተቆጣጣሪ አካል ለቁጥጥር ስራው መሳካት አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ አለባቸው፣

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
መዝገብ ቤት
Archive
Ethiopian Cooperative Commission Archive

Federal Democratic Ethiopia Kolata Primary SACCO Ltd

43.3. የኅብረት ስራ ማህበሩ በቁጥጥሩ ሪፖርት የተጠቀሱ የአሰራር ግድፈቶችን እና የሂሳብ ጉድለቶችንማረም አለበት፣

44. የኦዲትሪፖርትአያያዝ፣

የኅብረት ስራ ማህበሩ የኦዲት ሪፖርት ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ጋር የስራ ግንኙት ያላቸው አካላት በቀላሉ ሊያገኙትና ሊያዩት በሚችሉበት አኳኋን በጥንቃቄ መቀመጥ አለበት፣

45. የኅብረት ሥራ ማኅበሩ ንብረትና ገንዘብ ላይ ጉድለት ሲደርስ ስለሚወስድ እርምጃ ፣

45.1. የኅብረት ሥራ ማህበሩሥራ እንዲያካሂድ ኃላፊነት የተጣለበት ወይም ተጥሎበት የነበረው አባል፣አመራር ወይም ሠራተኛ የሚከተሉትን ጥፋት ፈጽሞ ከተገኘ፡-

45.1.1. ከኅብረት ሥራ አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያዎች እንዲሁም ከኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ውጪ ያልተፈቀደ ክፍያ ፈጽሞ ከተገኘ፣

45.1.2. እምነትን በማጉደል ወይም ሆን ብሎ በማሰብ ወይም በቸልተኝነት በኅብረት ሥራ ማህበሩ ንብረት ላይ ጉድለት አድርሶ ከተገኘ፣

45.1.3. የኅብረት ሥራ ማህበሩን ገንዘብ ያለአግባብ የወሰደ፣ የሸጠ፣ ያሸሸ፣ የደበቀ ወይም የሀሰት ማስረጃ ሰነድ ያቀረበ፣ ሰነዶችን ያጠፋ፣ የሰረዘ፣ የደለዘ፣ ወይም ሀሰት የሆነ የምስክር ወረቀት ያዘጋጀ ወይም ፈርሞ የሰጠ፣

45.1.4. የኅብረት ሥራ ማህበሩንብረት ወይም ገንዘብ በማጭበርበር ለራሱ ወይም ለሌላ ጥቅም ያዋለ ወይም ሌላ ሰው እንዲያጭበረብር ሁኔታዎችን በማመቻቸት የተባበረ እንደሆነ፣

45.1.5. በኅብረት ሥራ ማህበሩየፋይናንስ አሰራር መመሪያ ውስጥ ከተቀመጠው መስፈርት ውጭ የኅብረት ሥራ ማህበሩን አደጋ ላይ እንዲወድቅ ያደረገ፣በጋራም ሆነ በተናጠል ተጠያቂ ይሆናል፣

45.2. ተቆጣጣሪው ወይም መርማሪው ስለሁኔታው ዝርዝር ማስረጃዎችን በማዘጋጀት ለኅብረት ሥራ ማህበሩጠቅላላ ጉባኤ ወይም ለሥራ አመራር ኮሚቴ እና አግባብ ያለው ባለሥልጣን ሪፖርት ያደርጋል፡፡

45.3. ሪፖርት የቀረበለት አግባብ ያለው ባለሥልጣን ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው /ግለሰብ/ በሁለት ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ መልስ እንዲያቀርብ ዕድል ይሰጠዋል፡፡

45.4. ግለሰቡ በተሰጠው ጊዜ ገደብ መልስ ካልሰጠ የኅብረት ሥራ ማህበራት ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን ጉዳዩን በህግ እንዲጠየቅ ያደረጋል፣

46. የብድር ወይም እዳ አከፋፈል ቅደም ተከተል

ማንኛውም አባል በኅብረት ሥራ ማህበሩውስጥ ላለበት ብድር ወይም እዳ የአከፋፈል ቅደም ተከተል በሚከተለው ሁኔታ ይሆናል፡-

46.1. ወለድ የሚያስገኝ ክፍያዎች

46.1.1. ብድሩን ለመስጠት ለማስከፈል ለወጣው ወጪ ካሳ፣ ኪሳራ ቅጣት

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚ. መዝገብ ቤት Archive
Ethiopian Cooperative Commission Archive
The Federal Democratic Rep. Ethiopia Kefeta Youth Primary SACCO Ltd.

46.1.2. ለብድር ወለድ

46.1.3. ዋና ብድር ወይም እዳ ይሆናል፣

46.2. ወለድ አልባ ለሆነ ብድር

46.2.1. ለአባሉ የተሸጠበት ዋጋ ብቻ ነው፣

47. የኅብረት ሥራ ማህበሩውስጥ ስለሚነሳ አለመግባባት፣ በዕርቅ ስለመጨረስና ስለሽምግልና ዳኝነት፣

47.1. በኅብረት ሥራ ማህበሩውስጥ ለሚነሱ አለመግባባት በስራ አመራር ኮሚቴ ወይም በጠቅላላ ጉባኤ ታይቶ ውሳኔ ሲያገኝ ይችላል ።

47.2. ሆኖም ግን ውሳኔ ያላገኘ አለመግባባት በዕርቅ ወይም በሽምግልና ዳኝነት ማለቅ ይችላል፣ በዕርቅ ወይም በሽምግልና ዳኝነት የሚታዩ አለመግባባት በአዋጁ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናሉ፣

48. ስለኅብረት ሥራ ማህበራት መፍረስ፣

በሚከተሉት ምክንያቶች የኅብረት ሥራ ማህበሩሊፈርስ ይችላል፣

48.1. በኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ የኅብረት ሥራ ማህበር እንዲፈርስ ሲወስን

48.2. የአባላት ቁጥር ከ 100 በታች ሲሆን ፣

48.3. ፍርድ ቤት እንዲፈርስ ሲወስን ፣

48.4. በኅብረት ሥራ ማህበር ሂሳብ ምርመራ ውጤት መሰረት የከሰረና የኪሳራው መጠን የኅብረት ሥራ ማህበሩን ህልውና የሚያስጣ መሆኑን አግባብ ያለው ባለስልጣን ሲያረጋግጥና በጠቅላላ ጉባኤ ሲወሰን፣

48.5. ከአንቀጽ 47.1 እስከ 47.4 የተጠቀሱት ነጥቦች እንዳሉ ሆኖ የኅብረት ሥራ ማህበር እንዲፈርስ አግባብ ላለው ባለስልጣን ውሳኔውን በሰባት ቀናት ውስጥ እንዲያውቅ ይደረጋል፣

49. ሂሳብ አጣሪ ስለመመደብና ሌሎች መከናወን ያለባቸው ተግባሮች፣

49.1. የኅብረት ሥራ ማህበሩእንዲፈርስ ሲወሰን አግባብ ያለው ባለስልጣን በኅብረት ሥራ ማህበሩ ወጪ ሂሳብ አጣሪ ይመድባል፣

49.2. ሂሳብ አጣሪው የኅብረት ሥራ ማህበሩሂሳብ ያጣራል፣ ሀብት፣ዕዳና ንብረት ይለያል፣ ያሰባስባል፣ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ወክሎ በማናቸውም ጉዳዮች ይቀርባል፣

49.3. የገንዘብ ጠያቂዎች መብት መጠበቁ ከተረጋገጠ በኃላ የኅብረት ሥራ ማህበሩቀሪ ንብረት ለአባላት ባላቸው ዕጣ መሰረት ይከፋፈላል፣

49.4. ለኅብረት ሥራ ማህበሩየተሰጠውን የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምዝገባ ምስክር ወረቀት አግባብ ላለው ባለስለጣን ተመላሽ ያደርጋል፣ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ከተመለሰበት ቀን ጀምሮ የኅብረት ሥራ ማህበሩህጋዊ ሰውነት አይኖረውም፣

50. የመልካም ሥራ ዉጤት ማትጊያ አሰጣጥ፣

የኢትዮጵያ ... ሥራ ኮሚሽን
መዝገብ ቤት
Archive

...ederal Democratic ...
Ethiopia Kele...
Primary SACC...

50.1. የቅጥር ሠራተኛ በተነሳሽነትና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ የኅብረት ሥራ ማህበሩንዕድገት ማምጣት እስከቻሉ ድረስ ላከናወኑት ተግባር ከአመቱ ትርፍ ማትጊያ በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሠረት ሊከፈላቸዉ ይችላል፡፡

50.2. የኅብረት ሥራ ማህበሩአመራር አባላትና የቅጥር ሠራተኞች የመልካም ሥራ ዉጤት ማትጊያ የሚፈጸመው አግባብ ያለው አካል በሚያወጣው መመሪያ እና በኅብረት ሥራ ማህበሩየሰው ኃይል አስተዳደር መመሪያ መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፣

51. የውስጥ ደንብ ስለማውጣት፣

51.1. የሥራ አመራር ኮሚቴና የቁጥጥር ኮሚቴ በዚህ መተዳዳሪያ ደንብ መሰረት የውስጥ ደንብ አዘጋጅተው በጠቅላላ ጉባኤ አፀድቀው አግባብ ላለው ባለስልጠን አሳውቆ ስራ ላይ ማዋል አለበት፣

52. ስለ ደንብ ትርጓሜ፣

52.1. በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ አሻሚ የሆኑ ወይም ማብራሪያ የሚፈልጉ ወይም ክርክር የሚያስነሱ ቃላቶች ከተፈጠሩ አግባብ ያለው ባለስልጣን የመጨረሻ ይሆናል፣

53. **ልዩ ውሳኔ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች፣**

53.1. በአባላቱ ላይ አስገዳጅነት እንዲኖረው የሚያስፈልገው ልዩ ውሳኔ ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ውስጥ በሁለት ሶስተኛው መጽደቅ አለበት፣

53.2. የኅብረት ሥራ ማህበሩ መፍረስ፣ መተዳደሪያ ደንብ ሲጸድቅ፣መካፈል፣ መዋሀድና ሌሎች የኅብረት ሥራ ማህበሩን ህልውና አደጋ ላይ የሚጥሉ ጉዳዮች ልዩ ውሳኔ የሚያስፈልጋቸው ይሆናሉ፣

54. **የተመዳደሪያ ደንብ ስለማሻሻል፣**

54.1. ይህ መተዳደሪያ ደንብ ሊሻሻል የሚችለው በኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ቢያንስ በሁለት ሶስተኛው ድምፅ ሲፀድቅ መሆን አለበት፣

54.2. በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ የተደረገ መሻሻልና የኅብረት ሥራ ማኅበሩን ጠቅላላ ጉባኤ የተላለፈ ውሳኔ በሶስት ኮፒ ተዘጋጅቶ ውሳኔ ከተላለፈበት ጊዜ በ15 ቀን ውስጥ ለሚመለከተው አካል ቀርቦ ከተገመገመ በኋላ ተመዝግቦ ሕጋዊ ማህተም ተደርጎ ከተላከ በኋላ ሥራ ላይ ይውላል፡፡

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
መዝገብ ቤት
Archive
Ethiopian Cooperative Commission Archive

The Federal Democratic Rep. Ethiopia Kefeta Youth Primary SACCO Ltd.

55. **መተዳደሪያ ደንብ የሚፀናበት ጊዜ፣**

ይህ መተዳደሪያ ደንብ በኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ፀድቆ አግባብ ባለው አካል ቀርቦ ከተመዘገበበት

______________________ ቀን 2015 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አስተያየት የሰጠው አግባብ ያለው ባለስልጣን ባለሞያ

1. ስም------------------ ፊርማ------------------ ቀን------------------

የስራ አመራር ኮሚቴ አባላት ዝርዝር

1. ስም------------------ ፊርማ------------------ ቀን------------------
2. ስም------------------ ፊርማ------------------ ቀን------------------
3. ስም------------------ ፊርማ------------------ ቀን------------------
4. ስም------------------ ፊርማ------------------ ቀን------------------
5. ስም------------------ ፊርማ------------------ ቀን------------------
6. ስም------------------ ፊርማ------------------ ቀን------------------
7. ስም------------------ ፊርማ------------------ ቀን------------------
8. ስም------------------ ፊርማ------------------ ቀን------------------
9. ስም------------------ ፊርማ------------------ ቀን------------------

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚ... መዝገብ ቤት Archive Ethiopian Cooperative Commission

The Federal Democra... Ethiopia Kefet... Primary SACCO